በሁለተኛው ምዕራፍ የአጠቃላይ ትምህርት ጥራት ማሻሻያ ፕሮጀክት

የትምህርት ቤቶች ድጎማ በጀት

መመሪያ

በትምህርት ሚኒስቴር እና በትምህርት ዘርፍ የልማት አጋሮች አዘጋጅነት
በአጠቃላይ ትምህርት ጥራት ማሻሻያ ፕሮጀክት የፋይናንስ ድጋፍ የታተመ

ሰኔ 2007 ዓ.ም.

ምህፃረ ቃላት

አ.መ.ት.	አማራጭ መሠረታዊ ትምህርት
ፋ.ኢ.ል.ቢ.	የፋይናንስና ኢኮኖሚ ልማት ቢሮ
ት.አ.መ.ሥ.	የትምህርት አመራር መረጃ ሥርዓት
ት.ዘ.ል.ፕ.	የትምህርት ዘርፍ ልማት ፕሮግራም
አ.ት.ጥ.ማ.ፕ.	የአጠቃላይ ትምህርት ጥራት ማሻሻያ ፕሮግራም
ት.ሚ.	የትምህርት ሚኒስቴር
ዕ.ዝ.ሀ.ማ.ዳ.	የዕቅድ ዝግጅትና ሀብት ማፈላለግ ዳይሬክቶሬት
ወ.ተ.መ.ህ.	የወላጆች፣ ተማሪዎችና መምህራን ህብረት
ክ.ት.ቢ.	የክልል ትምህርት ቢሮ
ት.ቤ.ድ.በ.ፕ.	የትምህርት ቤቶች ድጎማ በጀት ፕሮግራም
ት.አ.ኮ.	የትምህርት ቤት አስተዳደር ኮሚቴ
ወ.ት.ጽ/ቤት	የወረዳ ትምህርት ጽ/ቤት
ወ.ፋ.ኢ.ል.ጽ/ቤት	የወረዳ ፋይናንስና ኢኮኖሚ ልማት ጽ/ቤት
ዞ.ት.ጽ/ቤት	የዞን ትምህርት ጽ/ቤት

ማውጫ

ምህፃረ ቃላት 2

መቅድም 6

በሁለተኛው ምዕራፍ የአጠቃላይ ትምህርት ጥራት ማሻሻያ ፕሮግራም (አ.ት.ጥ.ማ.ፕ/GEQIP II) የትምህርት ቤቶች ድጎማ በጀት አጠቃቀም የትኩረት አቅጣጫ ለውጥ 8

ክፍል 1፡ ስለ ትምህርት ቤቶች የድጎማ በጀት ፕሮግራም ማብራሪያ 10

1.1. የትምህርት ቤቶች የድጎማ በጀት ፕሮግራም ምንድን ነው? 10

1.2. የትምህርት ቤቶች የድጎማ በጀት ፕሮግራም ዋና ዋና ገጽታዎች ምንድን ናቸው? 11

1.3. የት/ቤቶች የድጎማ በጀት መጠን ምን ያህል ነው) 12

1.4. ለትምህርት ቤቶች የሚሰጠው የድጎማ በጀት በምን ሥራ ላይ ሊውል ይችላል 14

1.5. የትምህርት ቤቶች የገንዘብ አጠቃቀም ግምገማ 14

1.6. ማህበረሰብን በት/ቤቶች ድጎማ በጀት አጠቃቀም ላይ ክትትል እንዲያደርግና ተጠያቂነት እንዲኖር የሚያስችል የአሠራር ዘዴ (Social Accountability Mechanisms) 16

ክፍል 2፡ በፌደራል ደረጃ የሚሠራባቸው መመሪያዎች 18

2.1. የፌደራል ኃላፊነት 18

ተግባር 1: ተሻሽሎ የተዘጋጀውን የት/ቤቶች ድጎማ በጀት መመሪያ መተርጎምና ለሁሉም ክልሎች፣ ዞኖች፣ ወረዳዎች፣ ት/ቤቶችና አ.መ.ት.ማ. በየደረጃው በሚካሄዱ የስልጠና ዓውደ ጥናቶች አማካኝነት ማሰራጨት 18

ተግባር 2፡ በት/ቤት የድጎማ በጀት አጠቃቀም መመሪያ ላይ ለክልል አሰልጣኞች የስልጠና ወርክሾፕ ማደራጀት 19

ተግባር 3፡ ለት/ቤቶች የሚመደበውን የድጎማ በጀት ገንዘብ ለክልሎች የማስተላለፍ ሥራን ማስተባበር 20

ተግባር 4፡ የትምህርት ቤቶች የድጎማ በጀት አጠቃቀም ጥናቶች/ግምገማዎች ማካሄድና በግኝቶቹ ላይ የተመሠረቱ ዓውደጥናቶች ማካሄድ 20

ተግባር 5፡ ብሄራዊ (ሀገራዊ) የኮሙኒኬሽን ፕሮግራም/መድረክ ማመቻቸትና መተግበር፡፡ 21

ክፍል 3፡ በክልል ደረጃ የሚሠራባቸው መመሪያዎች 23

3.1. የክልሎች ኃላፊነት 23

ተግባር 1፡ የት/ቤት የድጎማ በጀት መመሪያን በሚመለከት በዞን እና በወረዳ ደረጃ የሥልጠና ወርክሾፖችን ማደራጀት/ማካሄድ 23

ተግባር 2: ወረዳዎች ልዩ ፍላጎት ላለባቸው ተማሪዎች የሚያስፈልጉ የትምህርት መሣሪያዎችን በማሟላት ድጋፍ ማድረግ እንዲችሉ ተብሎ የተመደበውን ተጨማሪ የትምህርት ቤቶች ድጎማ በጀት እንዲደርሳቸው ማድረግ፡፡ 24

ተግባር 3: የትምህርት ቤቶች ድጎማ በጀት የስርጭት/የድልድል ደብዳቤዎች በወቅቱ ለሚመለከታቸው ሁሉም ወረዳዎች እንዲደርሱ ማድረግ፡፡ 25

ተግባር 4፡ የት/ቤቶች የድጎማ በጀት ፕሮግራም ክትትልና ግምገማ ማካሄድ/መቆጣጠር 27

ክፍል 4፡ በዞን ደረጃ የሚሠራባቸው መመሪያዎች 28

4.1. የዞን ኃላፊነት 28

ተግባር 1፡ የወረዳ የት/ቤት የድጎማ በጀት ስልጠና ወርክሾፖችን በበላይነት ማስተባበር 28

ተግባር 2፡ የትምህርት ቤት የድጎማ በጀት ፕሮግራሙን መከታተል 28

ክፍል 5፡ በወረዳ ደረጃ የሚሰራባቸው መመሪያዎች 30

5.1. የወረዳ ኃላፊነት 30

ተግባር 1፡ የወረዳ የት/ቤት የድጎማ በጀት ስልጠና ወርክሾፖችን ማደራጀትና ማስተባር 30

ተግባር 2፡ ለትምህርት ቤቶችና የአ.መ.ት ማዕከላት የት/ቤት የድጎማ በጀት መመደብ 31

ተግባር 3፡ ልዩ ፍላጎት ላለባቸው ተማሪዎች የተመደበ ተጨማሪ በጀት ጭምር (ካለ) ለት/ቤቶችና አ.መ.ት. ማዕከላት የተመደበላቸውን የት/ቤቶች ድጎማ በጀት መጠን ማሳወቅ 37

ተግባር 4፡ ለትምህርት ቤቶችና የአ.መ.ት ማዕከላት የት/ቤት ድጎማ በጀት መስጠት 39

ተግባር 5፡ የት/ቤቶች ድጎማ በጀት ፕሮግራም አጠቃላይ ክትትል ማደረግ እንዲሁም ለት/ቤቶች እና አ.መ.ት. ማዕከላት ድጋፍ መስጠት 39

ክፍል 6 ፡ በት/ቤትና በህብረተሰቡ ደረጃ የሚሰራባቸው መመሪያዎች 41

6.1. የወ.ተ.መ.ህ ኃላፊነቶች 41

ተግባር 1፡ በት/ቤቶች ድጎማ ፕሮግራም አተገባበር ለወ.ተ.መ.ህ. ግንዛቤ ማስጨበጥና ለማህበረሰብ የግንዛቤ ማስፋፊያ መድረክ ማዘጋጀት 41

ተግባር 2፡ የት/ቤት ድጎማ በጀቱን በሚመለከት የወላጆችና የህብረተሰቡ ግንዛቤ ማስፊያ ስብሰባ ማዘጋጀት 43

ተግባር 3፡ ከት/ቤቶች የድጎማ በጀት ጋር የተያያዙ ሰነዶች በየጊዜው ማሻሻልና አደራጅቶ ማስቀመጥ 46

ተግባር 4፡ በት/ቤት መሻሻል ዕቅድ ውስጥ ልዩ ድጋፍ የሚያስፈልጋቸው ተማሪዎች ጉዳይ ማካተት (የልዩ ፍላጎት ተማሪዎች ካሉና ለዚህ የተመደበ በጀት ካለ) 48

ተግባር 5፡ የትምህርት ቤቶች ድጎማ በጀት ገንዘብን መቀበል 49

ተግባር 6፡ የትምህርት ቤት ማሻሻያ እቅዱን በሥራ ላይ ማዋል/መተግበር 50

ተግባር 7፡ የፋይናንስ አጠቃቀም ሁኔታን የሚገልፅ መረጃ በት/ቤቶች ድጎማ በጀት የማስታወቂያ ሰሌዳ መለጠፍ 51

አባሪዎች 52

አባሪ 1፡ በተለያዩ ደረጃዎች ላይ ያሉ ኃላፊነቶች የሚያሳይ ማጠቃለያ 52

አባሪ 2፡ የት/ቤት የሂሳብ ሪፖርት ቅጽ 53
አባሪ 3. የትምህርት ቤት ድጎማ በጀት መመደቢያ ቅፅ 55
አባሪ 4: የት/ቤት የቅድሚያ ትኩረቶች መለያ/ዝርዝር ማሳያ ቅጽ 56
አባሪ 5:የሁለተኛው ምዕራፍ አጠቃላይ ትምህርት ጥራት ማሻሻያ ፕሮጀክት የት/ቤቶች ድጎማ በጀት የሂሳብ መዝገብ ቅጽ 57
አባሪ 6: :የሁለተኛው ምዕራፍ አጠቃላይ ትምህርት ጥራት ማሻሻያ ፕሮጀክት የት/ቤቶች ድጎማ በጀት ማስታወቂያ ሰሌዳ ቅጽ 58

መቅድም

የትምህርት ቤቶች የድጎማ በጀት ፕሮግራም በትምህርት አደረጃትና አስተዳደር የህብረተሰብ ተሳትፎ እና ፋይናንስ መመሪያ ላይ በሰፈረው መሰረት በተማሪዎች ብዛት መጠን ለትምህርት ቤቶች ድጎማ በጀት የሚሰጥበትን ሥርዓት ለመደገፍ የተነደፈ የሁለተኛው ምዕራፍ አጠቃላይ ትምህርት ጥራት ማሻሻያ ፕሮግራም (አ.ት.ጥ.ማ.ፕ/GEQIP II) ክፍል ነው፡፡

የነፍስ ወከፍ በጀቱ በኢትዮጵያ ውስጥ በሚገኙ የአማራጭ መሰረታዊ ትምህርት ማዕከላት (አ.መ.ት) እና በመንግስትና በሕዝብ በሚተዳደሩ የመጀመሪያና የሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች ውስጥ የትምህርትን ጥራት ለማሻሻል እንዲቻል በትምህርት ቤቶች ደረጃ ከደመወዝ ውጪ የሆኑ መደበኛ ወጪዎችን ለመሸፈን ታስቦ የተዘጋጀ ነው፡፡ ይህንንም ተግባራዊ ለማድረግ ወላጆችና የህብረተሰቡ አባላት በትምህርት ቤቱ ውሳኔ አሰጣጥ ስርዓት በበጀት አጠቃቀምና በአፈጻጸም ቁጥጥር ላይ የበለጠ ንቁ ተሳትፎ እንዲኖራቸው ያስፈልጋል፡፡

ወላጆችና የህብረተሰቡ ክፍሎች በወላጆች፣ተማሪዎችና መምህራን ህብረት (ወተመህ) አማካኝነት ለትምህርት ቤቶች የተመደበው በጀት ለልጆቻቸው የሚቀርበውን የትምህርት ጥራት ለማሻሻል እንዴት እንደሚሠራበት በመወሰን ረገድ ቁልፍ ሚና ይጫወታሉ፡፡

የትምህርት ሚኒስቴር ለቀጣዮቹ አራት የሁለተኛው ምዕራፍ አጠቃላይ ትምህርት ጥራት ማሻሻያ ፕሮገራም (GEQIP II) የትግበራ ዓመታት፤ የሚቻል ከሆነም ከዚያ ለሚበልጥ ጊዜ በየዓመቱ ለአማራጭ መሰረታዊ ትምህርት ማዕከላት በመንግስትና በሕዝብ ለሚተዳደሩ ለሁሉም የየመጀመሪያ እና የሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች የሚያስፈልጋቸውን ዝቅተኛ ድጎማ በጀት በማስላት በጀት ይመደባል፡፡

ወላጆች በወ.ተ.መ.ህ በኩል በሚያደርጉት የጋራ ስምምነት መሠረት ለትምህርት ቤቶች የሚመደበው የድጎማ በጀት እንዴት ጥቅም ላይ እንደሚውል ይወስናሉ፡፡ የሚመደበው ድጎማ በጀት ለተለያዩ ዓይነት ዓላማዎች እንዲውል ታስቦ የሚሰጥ በመሆኑ እያዳንዱ ትምህርት ቤት ወይም የአማራጭ መሰረታዊ ትምህርት የትምህርትን ጥራት በማሻሻል

ረገድ የላቀ ውጤት ሊያመጡ በሚችሉና የቅድሚያ ትኩረት በሚሹ ተግባሮች ላይ ሊያውለው ይችላል፡፡

ወላጆች የትምህርት ቤቱን የድጎማ በጀት አጠቃቀም በሚመለከት እርዳታ የሚሹ ከሆነ ወይም በጀቱን በሚመለከት ጥያቄዎች ወይም ስጋቶች ካሏቸው በወ.ተ.መ.ህ. በኩል ለወረዳው የትምህርት ቢሮ ማሳወቃቸው በጣም አስፈላጊ ነው፡፡

ለትምህርት ቤቶች የሚመደበው የድጎማ በጀት ወላጆችና ህብረተሰቡ ለትምህርት ቤቶችና የአ.መ.ት. ማዕከላት በየዓመቱ ለሚሰጡት የገንዘብ ድጋፍ ማሟያ የሚሆን እንጂ የነበረውን የሚተካ አይደለም፡፡

በፌደራል፣ በክልል፣ በዞንና በወረዳ ደረጃዎች የሚገኙ ኃላፊዎች በዚህ መመሪያ ላይ በሰፈረው ዝርዝር መሰረት የየበኩላቸውን ድርሻና ኃላፊነት በአግባቡ መወጣት ይኖርባቸዋል፡፡

በፌደራል፣ በክልል፣ በዞን እና በወረዳ ደረጃ የሚሠሩ ሠራተኞች በትምህርት ቤቶች የድጎማ በጀት ፕሮግራም መመሪያ መሠረት የሚያወጡት ማንኛውም ወጪና የሚታየው ውጤት በአግባቡ መመዝገቡን ማረጋገጥ አለባቸው፡፡

የትምህርት ሚኒስቴር ወላጆች፣ የት/ቤቶች ርዕሰ መምህራን፣ መምህራን እና የማህበረሰቡ አባላት የትምህርት ቤቶችን ድጎማ በጀት በሥራ ላይ በማዋል ረገድ ለሚያከናውኑት ትጋት የተሞላበት ተግባር ምስጋናውን ይገልጻል፡፡

በሁለተኛው ምዕራፍ የአጠቃላይ ትምህርት ጥራት ማሻሻያ ፕሮግራም (አ.ት.ጥ.ማ.ፕ/GEQIP II) የትምህርት ቤቶች ድጎማ በጀት አጠቃቀም የትኩረት አቅጣጫ ለውጥ

በሁለተኛው ምዕራፍ የአጠቃላይ ትምህርት ጥራት ማሻሻያ ፕሮጀክት (GEQIP II) የት/ቤቶች ድጎማ በጀት አጠቃቀም የትኩረት አቅጣጫ ለውጥ ተደርጓል፡፡ ይኸውም በአሁኑ ወቅት የት/ቤቶች ድጎማ በጀት አሰተዳደርና አከፋፈል ጠንካራና እሰተማማኝ ስርዓት የተዘረጋ በመሆኑ በጀቱ ትምህርት ቤቶች ለይተው በሚያስቀምጡዋቸው በተሻለ ሁኔታ የተማሪዎችን ውጤት ማሻሻል በሚችሉ ቁልፍ ተግባራት ላይ እንዲውል ለማድረግ የሚያስችል ልዩ የትኩረት እቅጣጫ ተቀምጧል፡፡ የትምህርት ቤቶች ዋና ትኩረት ተማሪዎች በዕውቀት፣ በግንዛቤ እና በክህሎት ተገቢው ብቃት እንዲኖራቸው ማስቻል ነው፡፡ ይህ ማለት ደግሞ የሚከተሉትን ሁለት የአሠራር ዘዴዎች ለውጥን ያሳያል፡፡

1. **ትምህርት ቤቶች ከሚሰጣቸው የድጎማ በጀት ላይ ቢያንስ 50% ያህል በት/ቤት መሻሻል ዕቅዶቻቸው ተለይተው በተቀመጡ የመማርና ማስተማር ርዕሰ ጉዳይ** (teaching and learning domain) **ተግባሮች ላይ ማዋል ይኖርባቸዋል፡፡**
2. **የት/ቤት መሻሻል ዕቅዶች በተጨባጭ ማስረጃ ላይ የተመሠረቱ መሆን ይኖርባቸዋል፡፡** የወላጆች፣ የተማሪዎችና የመምህራን ህብረቶች የየት/ቤቶቻቸውን ዕቅዶች ሲያዘጋጁ የመማርና ማስተማር ተግባሩን ውጤታማ ለማድረግ የሚረዱ ተግባሮችን ለመለየት እንዲያስችላቸው፤ የሁሉም ትምህርት ዓይነቶች የተማሪዎች ውጤት፣ የተማሪዎች በክፍል ውስጥ መኖርና አለመኖር፣ የተማሪዎች በክፍል መድገምና ማቋረጥ መጠን፣ የመማሪያና ማስተማሪያ ቁሳቁሶች አቅርቦት፣ እንዲሁም ከመምህራንና ከተማሪዎች የሚሰበሰቡ ከመማርና ማስተማር መስተጋብር ጋር አግባብነት ያላቸውን መረጃዎች መጠቀም ይኖርባቸዋል፡፡

በመረጃ ላይ የተመሠረተ ዕቅድ ማዘጋጀትና በዕርዳታ የተገኘውን ገንዘብ በመማርና ማስተማር ርዕሰ ጉዳዮች ላይ ዒላማ ማድረግ ማለት የት/ቤቶች ድጎማ በጀት ት/ቤቶችን በአፋጣኝ የሁሉም ተማሪዎች ውጤት እንዲሻሻል ለማድረግ በሚያስችል ሥራ ላይ እንዲያውሉት ይረዳቸዋል ማለት ነው፡፡

ትም/ቤቶች የመማር ማስተማሩን ሁኔታ ለማሻሻል ከዚህ በታች የተዘረዘሩትን ተግባራት ትኩረት ሰጥተው እንዲተገብሩዋቸው ይጠበቃል፡፡

- የመምህራን ዕውቀት፣ ክህሎትና ግንዛቤን ማሻሻል
- የስርዓተ ትምህርት ቁሳቁሶች/ማቴሪያሎች (መርሀ ትምህርት፣ የተማሪ መፅሐፍ፣ የመምህሩ መመሪያ፣ ማጣቀሻ እና የትምህርት መርጃ መሣሪያዎች) አቅርቦትና አጠቃቀም ማሻሻል
- መምህራን ተከታታይ የሙያ ማሻሻያ ስልጠናዎች ማግኘት የሚችሉበት የአሠራር ስርዓትና አመቺ ሁኔታ ማሻሻል
- ተማሪዎች ግንዛቤአቸውን ለማሻሻል በሚረዱዋቸው የት/ቤት ክበቦች እና በሌሎች ተጓዳኝ ማህበረሰብ አቀፍ ተግባሮች ላይ የሚኖራቸው ንቁ ተሳትፎ ማሻሻል
- ተማሪዎች በሚማሩዋቸው ትምህርቶች ላይ ከነባራዊ ህይወታቸው ጋር በማገናዘብ/በማነፃፀር ግብረ መልስ እንዲሰጡ ማሳተፍ
- አሳታፊ ወይም ተማሪን ማዕከል ያደረገ የማስተማር ዘዴን በመጠቀም በክፍል ወስጥ (በመማርና ማስተማር ሂደት) የተማሪዎችን ተሳትፎ ማሻሻል
- መምህራን የተማሪዎቻቸውን ዕድሜና ደረጃ ከግምት ውስጥ በማስገባት ተገቢ/ተስማሚ የሆኑ የምዘና ዘዴዎችን እንዲጠቀሙ ማድረግ
- ገንቢ እሰተያየቶቻቸውን ማስቀመጥ ይችሉ ዘንድ፣ ለወላጆች ወቅታዊ የልጆቻቸውን ባህሪያትና የብቃት ደረጃዎች ለውጦችን የሚሳዩ ሪፖርቶች ማቅረብ
- አግባብ ያላቸው የትምህርት ሙያ ማሻሻያ ማዕከሎች ቁሳቁሶች፣ የቤተ ሙከራ ቁሳቁሶች፣ የሳይንስ መሣሪያዎች ጥቅል/ኪት እና አጋዥ የንባብ መፃሕፍት መምረጥና መጠቀም

ክፍል 1፡ ስለ ትምህርት ቤቶች የድጎማ በጀት ፕሮግራም ማብራሪያ

1.1. የትምህርት ቤቶች የድጎማ በጀት ፕሮግራም ምንድን ነው?

- የትምህርት ቤቶች ድጎማ በጀት ፕሮግራም (ት.ቤ.ድ.በ.ፕ) በኢትዮጵያ መንግስትና በልማት አጋሮች በተነደፈው ሁለተኛው ምዕራፍ የአጠቃላይ ትምህርት ጥራት ማሻሻያ ፕሮግራም (አ.ት.ጥ.ማ.ፕ) ሥር የሚተዳደር ሆኖ በሁሉም የመንግስት የመጀመሪያና ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች እንዲሁም በአማራጭ መሠረታዊ ትምህርት መስጫ ማዕከላት ዘንድ የትምህርት አሠጣጥ አፈፃፀም ብቃት ለማጎልበትና የትምህርት ጥራትን ለማሻሻል የተነደፈ መርሃ ግብር ነው፡፡
- የትምህርት ቤቶች ድጎማ በጀት በሚኖሩዋቸው ተማሪዎች ብዛት መሠረት በአገሪቱ ለሚገኙ ሁሉም የአማራጭ መሠረታዊ ትምህርት ማዕከላት (አ.መ.ት.ማ.) እና የመንግስት የመጀመሪያና ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች የሚመደብ/የሚሰጥ ገንዘብ ነው፡፡
- የትምህርት ቤቶች ድጎማ በጀት ለመማር እና ማስተማር ተግባራት መሻሻል ልዩ ትኩረት በመስጠት በወ.ተ.መ.ህ. ወሳኝነት ትምህርት ቤቶች የትምህርት ቤት መሻሻል ዕቅዶቻቸውን ለመተግበርና የአፈፃፀም ብቃታቸውን ለማሻሻል የሚጠቀሙበት ገንዘብ ነው፡፡
- በሁለተኛው ምዕራፍ የአጠቃላይ ትምህርት ጥራት ማሻሻያ ፕሮግራም ለመማር እና ማስተማር ተግባራት ልዩ ትኩረት የተሰጠው በመሆኑ ትም/ቤቶች ከሚመደብላቸው የድጎማ በጀት ውስጥ ቢያንስ 50% ያህል በትምህርት ቤት መሻሻል ዕቅዶቻቸው ለመማርና ማስተማር ርዕሰ ጉዳዮች/ መጠቀም ይኖርባቸዋል፡፡
- የትምህርት ቤቶች ድጎማ በጀት ወላጆችና ህብረተሰቡ ለትምህርት ቤቶችና የአ.መ.ት. ማዕከላት በየዓመቱ ለሚሰጡት የገንዘብ ድጋፍ ማሟያ የሚሆን እንጂ የነበረውን አሰራር የሚተካ አይደለም፡፡ የትምህርት ቤቶች ድጎማ በጀት ት/ቤቶች የመማር ማስተማሩን ሥራ/ሁኔታ ለማሻሻል እንዲረዳቸው የሚመደብ ተጨማሪ ገንዘብ ነው፡፡

1.2. የትምህርት ቤቶች የድጎማ በጀት ፕሮግራም ዋና ዋና ገጽታዎች ምንድን ናቸው?

የሥራ አመራር/የትምህርት ቤቶች ድጎማ በጀት አስተዳደር (Management)	የትምህርት ቤቶች ድጎማ በጀት በሚከተሉት 5 እርከኖች/ደረጃዎች ይተዳደራል፡፡ (1) ፌደራል፣ (2) ክልል፣ (3) ዞን፣ (4) ወረዳ፣ እና (5) ት/ቤትና ማህበረሰብ ናቸው፡፡ የወ.ተ.መ.ህ. በት/ቤቶች እና በአማራጭ የመሠረታዊ ትምህርት መስጫ ማዕከላት የድጎማ በጀቱን በማስተዳደር ቁልፍ ሚና ይጫወታሉ፡፡ የእያንዳንዱ እርከን/ደረጃ ሃላፊነትም በአባሪ 1 ላይ ተዘርዝሯል፡፡
የትምህርት ቤቶች ድጎማ በጀት መሰጠት የሚገባቸው የትምህርት ተቋማት (Eligibility)	የትምህርት ሚኒስቴር ለሁሉም በአገሪቱ የሚገኙት የመንግስት የመጀመሪያና ሁለተኛ ደረጃ ት/ቤቶች እንዲሁም የአማራጭ መሠረታዊ ትምህርት መስጫ ማዕከላት በፕሮጀክቱ ለዚሁ ተግባር የተመደውን ገንዘብ ይሰጣል፡፡
በነፍስወከፍ ተማሪ የትምህርት ቤቶች ድጎማ በጀት መጠን (Amount per student)	በሁለተኛው ምዕራፍ የአጠቃላይ ትምህርት ጥራት ማሻሻያ ፕሮግራም (GEQIP-II) ለትምህርት ቤቶች የሚመደበው የትምህርት ቤቶች ድጎማ በጀት ዝቅተኛ መጠን ያለው በጀት ሲሆን ዝርዝሩ በዚሁ መመሪያ ክፍል አንድ ንዑስ ክፍል 1.3 ላይ ቀርቧል፡፡ የሚመደበው በጀት በትምህርት እርከን/ደረጃ የሚለያይ ነው፡፡ ትምህርት ቤቶችና የአ.መ.ት ማዕከላት በትምህርት አደረጃጀትና አስተዳር መመሪያ ላይ የተቀመጠውን የበጀት መጠን ለማሟላት እንዲችሉ ወረዳዎች ተጨማሪ የገንዘብ ድጎማ እንዲያደርጉላቸው በእጅጉ ይበረታታሉ፡፡
የትምህርት ቤቶች ድጎማ በጀት አመዳደብ የመረጃ ምንጭ (Allocation)	የትምህርት ቤቶች የድጎማ በጀት አመዳደብ ከፌደራል የትምህርት ሥራ አመራር መረጃ ሥርዓት (EMIS) በተገኘ የተማሪዎች ምዝገባ መረጃ ላይ ተመርኩዞ የሚደለደል/የሚፈፀም ነው፡፡ የምዝገባ መረጃዎችን ለማሰባሰብና ለማጠናቀር በሚፈጀው ጊዜ ወቅታዊ የሆኑ መረጃዎችን ለማግኘት ሚያጋጥሙ ችግሮች ምክንያት ሁልጊዜ ስሌቱ የሚመሰረተው ሁለት አመታት ቀደም ብሎ በተሰበሰበው መረጃ ሲሆን በየዓመቱ ይጨምራል ተብሎ የሚገመተውን የተማሪ ብዛት ከግምት ውስጥ በማስገባት ነው፡፡ ለምሳሌ የ2008 ዓ.ም. የት/ቤቶች ድጎማ በጀት መሠረት ያደረገው በ2006 ዓ.ም. የነበረውን የተማሪዎች ብዛት ሲሆን በየዓመቱ ለሚከሰተው የተማሪዎች ቁጥር ዕድገት ተጨማሪ የመጠባበቂያ ገንዘብ እንዲካተት ተደርጓል፡፡ ለመጠባበቂያ የተካተተውን የገንዘብ መጠን በዝርዝር ለመገንዘብ ሰንጠረዥ 3 ይመልከቱ፡፡
የትምህርት ቤቶች ድጎማ በጀት አከፋፈል (Disbursement)	የት/ቤቶች የድጎማ በጀት ለሁሉም ት/ቤቶችና የአማራጭ መሠረታዊ ትምህርት መስጫ ማዕከላት በዓመት አንድ ጊዜ የሚመደብ/የሚከፈል ሲሆን ከልማት አጋር ድርጅቶች ለዚሁ ተግባር ተጨማሪ ገንዘብ ሲገኝ በማንኛውም የትምህርት ዘመን ወቅት/ወር ተጨማሪ የድጎማ በጀት ሊላክላቸው ይችላል፡፡ የሚላከው/የሚመደበው የት/ቤቶች ድጎማ በጀት በየዓመቱ እ.ኤ.አ. ኦክቶበር 31 ላይ በየትምህርት ተቋማቱ መድረስ ይኖርበታል፡፡ በጀቱ ከፌደራል ወደ ክልሎች የሚላክ ሲሆን የክልል ፋይናንስና ኢኮኖሚ ልማት ቢሮዎች ገንዘቡን ለወረዳ ፋይናንስና ኢኮኖሚ ልማት ጽ/ቤቶች ይልካሉ፡፡ የወረዳ ፋይናንስና ኢኮኖሚ ልማት ጽ/ቤቶችም ባንኮች በሚኖሩባቸው የት/ቤቶች አካባቢዎች የባንክ ሂሳብ በመክፈት፤ ባንኮች በማይኖሩባቸው አካባቢዎች ደግሞ በካሽ አማካኝነት ገንዘቡ ወደሚመለከታቸው የትምህርት ተቋማት እንዲደርስ ያደርጋሉ፡፡
አተገባበር/አፈፃፀም (Implementation)	እያንዳንዱ ትምህርት ቤት ወይም አ.መ.ት. ማዕከል የተመደበለት የድጎማ በጀት የትምህርት ቤት ማሻሻያ ዕቅዱን ለመተግበርና የትምህርት ቤቱን የማስተማር ብቃት ለማሳደግ የሚጠቀምበት ሲሆን በተለይም የትምህርት ጥራት ለማሻሻል ልዩ ትኩረት ያደርጋል፡፡ በእያንዳንዱ ት/ቤት ወይም አ.መ.ት. ማዕከል የተላከው የት/ቤቶች ድጎማ በጀት መቼ እንደደረሰ፣ መጠኑ ምን ያል እንደሆነ፣ እንዲሁም ለምን ተግባር መዋል እንዳለበት የሚገለጽበትና ወላጆች እና የማህበረሰብ አባላት በቀላሉ ሊያዩት በሚችሉበት ቦታ ላይ ያለ በተለይ ለት/ቤቶች ድጎማ በጀት የተዘጋጀ የማስታወቂያ ሰሌዳ መኖር አለበት፡፡

1.3. የት/ቤቶች የድጎማ በጀት መጠን ምን ያህል ነው)

- የትምህርት ሚኒስቴር በእያንዳንዱ የአ.መ.ት.ማዕከል እንዲሁም የመጀመሪያና ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት በሚገኙ/በተመዘገቡ ተማሪዎች ቁጥር ልክ መከፈል የሚገባውን ዝቅተኛ የገንዘብ መጠን ወስኗል፡፡ ይህ መጠን 'መደበኛ' የት/ቤቶች ድጎማ በጀት በመባል ይታወቃል፡፡ ትም/ቤቶች ፍላጎቶቻቸውን ማሟላት/የቅድሚያ ትኩረት ተግባሮቻቸውን ለመከወን ይችሉ ዘንድ ወረዳዎች ተጨማሪ ድጋፍ እንዲያደርጉላቸው በእጅጉ ይበረታታሉ፡፡ ሰንጠረዥ 1 ለእያንዳንዱ የትምህርት እርከን የተፈቀደውን መደበኛ የትምህርት ቤቶች ድጎማ በጀት ዝርዝር ያሳያል፡፡ የትምህርት ተቋማቱ በሚኖሩዋቸው ተማሪዎች ብዛትና ዝቅተኛ ማግኘት የሚገባቸው የትምህርት ቤቶች ድጎማ በጀት አመዳደብ ምሳሌም በሰንጠረዥ 2 ላይ ቀርቧል፡፡

ሰንጠረዥ 1፡ በተለያዩ የትምህርት እርከኖች (የክፍል ደረጃዎች) በነፍስ ወከፍ ተማሪ የሚመደብ ዝቅተኛው መደበኛ የት/ቤቶች ድጎማ በጀት

ከ1ኛ-4ኛ ክፍል	ከ5ኛ-8ኛ ክፍል	የአማራጭ መሠረታዊ ትምህርት መስጫ ማዕከል	ከ9ኛ-10ኛ ክፍል	ከ11ኛ-12ኛ ክፍል
ብር 50	ብር 55	ብር 50	ብር 60	ብር 70

ሰንጠረዥ2፡ በተለያዩ የክፍል ደረጃዎች በተማሪዎች ቁጥር መሰረት የሚሰጠውን የድጎማ በጀት የሚያሳይ ምሳሌ *(ለተጨማሪ መረጃ በግርጌ ማስታወሻ የቀረበውን የአመዳደብ ቀመር ይመልከቱ)*[1]

ተ.ቁ.	የትምህርት ተቋሙ ዓይነት/ደረጃ (ምሳሌ)	ት/ቤቱ ያሉት የክፍል ደረጃዎች	የተመዘገቡ ተማሪዎች ቁጥርና በነፍስ ወከፍ ለተማሪዎች የተመደበ መደበኛ የድጎማ በጀት (ብር)					ድምር (ለት/ቤቶች የሚደርሳቸው የድጎማ በጀት መጠን) (ብር)
			ከ1ኛ-4ኛ	ከ5ኛ-8ኛ	አ.መ.ት.መ	ከ9ኛ-10ኛ	ከ11ኛ-12ኛ	
			ብር 50	ብር 55	ብር 50	ብር 60	ብር 70	
1	የመጀምሪያ ደረጃ ት/ቤት	1-4	350	-	-	-	-	17,500
2	የመጀመሪያ ደረጃ ት/ቤት	1-8	215	115	-	-	-	17,075
3	አ.መ.ት ማዕከል	1፣2፣3	-	-	460	-	-	23,000
4	ሁለተኛ ደረጃ ት/ቤት	9-12	-	-	-	850	340	74,800
5	ሁለተኛ ደረጃ ት/ቤት	11-12	-	-	-	-	470	32,900

[1] (1) 350 ተማሪዎች * ብር 50 = ብር 17,500፣ (2) (215 ተማሪዎች* ብር 50) + (115 ተማሪዎች * ብር 55) = ብር 17,075፣ (3) 460 ተማሪዎች * ብር 50 = ብር 23,000፣ (4) (850 ተማሪዎች * ብር 60) + (340 ተማሪዎች * 70 ብር) = ብር 74,800፣ (5) 470 ተማሪዎች* ብር 70 = 32,900 ብር.

- ከመደበኛው የት/ቤቶች ድጎማ በጀት በተጨማሪ ብዛታቸው ከ200 በታች ተማሪዎች ላሉዋቸው ት/ቤቶች በተለየ መልኩ 200 ተማሪዎች እንዳሉዋቸው ታሳቢ በማድረግ ተጨማሪ የት/ቤቶች ድጎማ በጀት የሚመደብላቸው ሲሆን ስሌቱ በሰንጠረዥ 3 ቀርቧል፡፡

ሰንጠረዥ 3: የት/ቤቶች ድጎማ በጀት መጠባበቂያና ተጨማሪ ክፍያ ስሌት

ከ200 ተማሪዎች በታች ያሉዋቸው ት/ቤቶች	ከ200 በታች ተማሪዎች ያሉዋቸው ት/ቤቶች በተለየ መልኩ 200 ተማሪዎች እንዳሉዋቸው ታሳቢ በማድረግ የት/ቤቶች ድጎማ በጀት ተሰልቶ ይመደብላቸዋል፡፡ ይህ ሁኔታ እያንዳንዱ አ.መ.ት.ማ. ወይም ት/ቤት በት/ቤት መሻሻል ዕቅድ ላይ የተለዩትን የቅድሚያ ትኩረቶችን በበቂ ሁኔታ ለማከናወን/ለመተግበር የሚያስችል ዝቅተኛ የገንዘብ መጠን መመደቡን ያረጋግጣል፡፡ ይህ በልዩ ሁኔታ የተመደበው ገንዘብ በአመዛኙ በገጠር አካባቢዎች በሚገኙትና ዝቅተኛ ተደራሽነት ባለባቸው ትንንሽ ት/ቤቶችና አ.መ.ት.ማ. የሴቶችን ተሳትፎ በማሻሻልና ትምህርት ለሁሉም በማዳረስ ረገድ አዎንታዊ ተፅዕኖ እንደሚያሳድር ይታመንበታል፡፡ የተማሪዎችን ብዛት መሠረት ያደረገ መደበኛ የት/ቤቶች ድጎማ በጀት ከጠቀም ይልቅ ከ200 ተማሪዎች በታች ላሉዋቸው ት/ቤቶች ከዚህ በታች የቀረበውን ስሌትና አንድ ዓይነት የገንዘብ መጠን መጠቀም ጥሩ አማራጭ እንደሆነ ታምኖበታል፡፡ – **አንደኛ ደረጃ: ብር** 10,000 *(ብር 50 x 200 ተማሪዎች)* – **ሁለተኛ ደረጃ: ብር** 12,000 *(ብር 60 x 200 ተማሪዎች)* – **አ.መ.ት.ማ.: ብር** 10,000 *(ብር 50 x 200 ተማሪዎች)* የት/ቤቶች ድጎማ በጀቱ ስሌት ካለው ተጨባጭ የተማሪ ብዛት በላይ ሆኖ ሲገኝ ከፍተኛው መጠን ይወሰዳል/ጥቅም ላይ ይውላል፡፡
በየዓመቱ ሊከሰት የሚችለውን የተማሪዎች ብዛት መጨመር ምክንያት በማድረግ የሚመደብ ተጨማሪ/መጠባበቂያ የት/ቤቶች ድጎማ ገንዘብ (Contingency for increased enrolment between allocation and receipt of school grant)	ከላይ እንደተጠቀሰው የት/ቤቶች ድጎማ በጀት ምደባ/ስሌት የተመሰረተው ከሁለት ዓመታት በፊት በነበረው የትምህርት አመራር መረጃ ስርዓት ሪፖርት በሚያመለክተው የተማሪዎች ብዛት ስለሆነ በየዓመቱ ሊከሰት የሚችለውን የተማሪዎች ብዛት መጨመር ከግምት ውስጥ በማስገባትና ተጨማሪውን በማስላት ት/ቤቶች የተመደበላቸውን የድጎማ በጀት በየዓመቱ መጀመሪያ ማግኘት እንዲችሉ ተደርጓል፡፡ ጭማሪው/መጠባበቂያው በወረዳ ደረጃ ተሰልቶ የተመደበ ሲሆን የወረዳ ትምህርት ጽ/ቤቶች ይህንኑ በመገንዘብ ለሚመለከታቸው የተማሪ ቁጥር ዕድገት ላሳዩና አዲስ ለተከፈቱ ት/ቤቶች መመሪያውን በመከተል መመደብ ይኖርባቸዋል፡፡ ባለፉት ዓመታት በየዓመቱ የጨመረውን የተማሪዎች ቁጥር ከግምት ውስጥ በማስገባት ተጨማሪ/መጠባበቂያ የት/ቤቶች ድጎማ በጀት ምደባ እንደሚከተለው ተሰልቷል፡፡ – **ለታዳጊ ክልሎች (አፋር፣ ኢትዮጵያ ሱማሌ፣ ጋምቤላና ቤንሻንጉል ጉሙዝ):- ለሁሉም ወረዳዎች በ2006 ዓ.ም የተማሪዎች ብዛት መነሻነት** 15% መጠባበቂያ የድጎማ በጀት ይጨመራል/ይካተታል፡፡ – **ለተቀሩት 5 ክልሎችና 2 የከተማ አስተዳደሮች (ኦሮሚያ፣ ትግራይ፣ ደቡብ፣ አማራ፣ ሀረሪ፣ አዲስ አበባና ድሬዳዋ): ለሁሉም ወረዳዎች በ2006 ዓ.ም. የተማሪዎች ብዛት መነሻነት** 10% መጠባበቂያ የድጎማ በጀት ይጨመራል/ይካተታል፡፡
ልዩ ፍላጎት ላላቸው ህፃናት የተመደበ ተጨማሪ የት/ቤቶች ድጎማ በጀት (Top-up to support the education of children with Special Educational Needs)	ልዩ ፍላጉት ያላቸውን ህፃናት በትምህርት ድጋፍ ለማድረግና አመቺ የትምህርት አካባቢ እንዲኖራቸው ለመርዳት እንዲሁም የት/ቤቶች መገልገያዎች ለእነዚህ ህፃናት አመቺ እንዲሆኑ ለማድረግ ከላይ በተጠቀሰው መረጃ መነሻነት ለሁሉም ክልሎች ተጨማሪ 1% የት/ቤቶች ድጎማ በጀት እንዲመደብ ተደርጓል፡፡ ልዩ ፍላጎት ያላቸው ህፃናት ያሉባቸው ት/ቤቶችና ወረዳዎች እንደየክልሉ ነባራዊ ሁኔታ ሊለያይ ስለሚችል የክልል ት/ቢሮዎች ይህንኑ በወረዳና በት/ቤት ደረጃ የመለየትና የመመደብ ሃላፊነት አለባቸው፡፡ ይህ ሁኔታ የኢትዮጵያ መንግሥት የትምህርቱን ስርዓት አካታችነት ለማሻሻል ጠንክሮ እንደሚሠራ ከሚያመለክቱ ተግባሮች አንዱ መሆኑን ያሳያል፡፡

1.4. ለትምህርት ቤቶች የሚሰጠው የድጎማ በጀት በምን ሥራ ላይ ሊውል ይችላል

- እያንዳንዱ የአ.መ.ት.ማ. እና ት/ቤት የሚመደብለትን የት/ቤቶች ድጎማ በጀት የትምህርት ተቋሙን የት/ቤት መሻሻል እቅድ ለመተግበር በተለይም ለመማርና ማስተማር ሂደት ልዩ ትኩረት በመስጠት የትምህርት ጥራትን ለማሻሻል ብርቱ ጥረት ማድረግ ይጠበቅበታል፡፡
- ት/ቤቶች ከሚሰጣቸው የት/ቤት ድጎማ በጀት ውስጥ ቢያንስ 50% የሚሆነውን በት/ቤት መሻሻል መርሀ ግብር ለመማር ማስተማር ርዕሰ ጉዳይ (domain) ማዋል ይኖርባቸዋል፡፡
- የት/ቤቶችን ድጎማ በጀት ከዚህ በታች በቀረበው ሰንጠረዥ (ሰንጠረዥ 4) ላይ ለተዘረዘሩት 5 ተግባሮች መጠቀም አይፈቀድም፡፡ ወ.ተ.መ.ህ. በዝርዝሩ የተካተቱትን/የተጠቀሱትን ተግባሮች ማከናወን ከፈለጉ፣ እንደ ማህበረሰብ መዋጮ የመሳሰሉ ሌሎች የገንዘብ ምንጮች መጠቀም ይችላሉ፡፡

ሰንጠረዥ 4፡ የት/ቤቶች ድጎማ በጀትን መጠቀም የማይፈቀድባቸው ተግባራት

ተ.ቁ	ተግባር
1	አዳዲስ መማሪያ ክፍሎችንና ሕንፃዎችን ለመገንባት (አዳዲስ መጸዳጃ ቤቶችን መገንባት ግን ይቻላል)
2	ደመወዝ፣ የውሎ አበልና ለግለሰቦች የሚሰጥ ክፍያ
3	ቴሌቭዥኖችና የዲቪዲ ማጫወቻዎች
4	ነዳጅ
5	የጦር መሳሪያዎች

1.5. የትምህርት ቤቶች የገንዘብ አጠቃቀም ግምገማ

- በየዓመቱ በሀገሪቱ ካሉ አማራጭ መሰረታዊ ትምህርት ማዕከላትናመደበኛ ት/ቤቶች 3 በመቶ (3%) ያህሉን በናሙናነት በመውሰድ የተመደበው የድጎማ በጀት በተገቢው ሥራ ላይ መዋሉን ለማረጋገጥና ቁጥጥር ለማድረግ እንዲረዳ የሒሳብ ምርመራ ይካሄዳል፡፡ የሒሳብ ምርመራው በት/ቤቶች ድጎማ መመዝገቢያ ደብተርና ሌሎች ደጋፊ ሰነዶች ላይ የሚካሄድ ሲሆን የሂሳብ ምርመራ ባለሙያዎች እንደ አስፈላጊነቱ ናሙና ት/ቤቶችንና አ.መ.ት.ማ. እንዲሁም ወረዳዎችን በመጎብኘት ምርመራውን ያካሂዳሉ፡፡ የምርመራ/ኦዲት ሥራው የሂሳብ ምርመራ አገልግሎት የአሠራር ሂደትን

ተከትሎ የሚፈፀም ሲሆን በአባሪ 2 ላይ በቀረበው የትምህርት ቤት የገንዘብ አጠቃቀም ግምገማ ሰነድ ላይ ባለው አሰራር መሰረት የሚካሄድ ይሆናል፡፡

- የት/ቤት በጀት አጠቃቀምን በሚመለከት አግባብነት የሌላቸው አሠራሮች በሚታዩበት ጊዜ የሚከተሉትን የማስተካከያ እርምጃዎች መውሰድ ይቻላል፡፡
    1. ትምህርት ቤቶች ከመዘገቧቸው ተማሪዎች የሚበልጥ ቁጥር ሪፖርት ሲያደርጉ፡፡ እንዲህ ያለ ሁኔታ ሲያጋጥም የወረዳው የትምህርት ጽ/ቤት እና የወ.ፋ.ኢ.ል.ጽ/ቤት የትምህርት ቤቱን ርዕሰ መምህር በማነጋገር ተገቢውን ማስተካከያ ያደርጋሉ፡፡
    2. ለትምህርት ቤቱ የተመደበውን የድጎማ በጀት አላግባብ መጠቀም፡- ይህ ሁኔታ ሲከሰት ሕግን እንደመጣስ ተደርጎ የሚቆጠር በመሆኑ መጀመሪያ የወላጅ፣ የተማሪና የመምህር ሕብረት (ወ.ተ.መ.ህ.) ጉዳዩን ለማስተካከል እርምጃ የሚወስዱ ሲሆን የወረዳና የክልል ቢሮዎችም እንደአስፈላጊነቱ እርምጃ ይወስዳሉ፡፡
    3. ት/ቤቶች እና አ.መ.ት.ማ. የድጎማ በጀት የሒሳብ መዝገባቸውንና ሌሎች ደጋፊ ሰነዶችን (ደረሰኞች፣ የክፍያ፣ የመቀበያ ሰነዶች) በሚገባ በማደራጀት በት/ቤቶች ድጎማ በጀት ማህደር/ፋይል ሳያስቀምጡ በሚቀሩበት ጊዜ የወረዳ ትምህርትና የገንዘብና ኢኮኖሚ ልማት ጽ/ቤቶች የሂሳብ ምርመራ ባለሙያዎች/ኦዲተሮች እና ኢንስፔክተሮች አስፈላጊውን መረጃ ማግኘት ስለማይችሉ እንዲህ ዓይነት ሁኔታ ሲፈጠር ለተገቢው እርምጃ የክልል ት/ቢሮዎችን ማሳወቅ ያስፈልጋል፡፡

1.6. ማህበረሰብን በት/ቤቶች ድጎማ በጀት አጠቃቀም ላይ ክትትል እንዲያደርግና ተጠያቂነት እንዲኖር የሚያስችል የአሠራር ዘዴ (Social Accountability Mechanisms)

- በዚህ መመሪያ ክፍል 1፣ ንዑስ ክፍል 1.2. ከቀረበው የትምህርት ቤቶች ድጎማ በጀት አስተዳደር በተጨማሪ ማህበረሰቡ ሊጫወተው የሚገባ የሃላፊነት ሚናን ሰፋ በማድረግ የአካባቢው ማህበረሰብ ሚና በትምህርት ቤቶች ድጎማ በጀት አጠቃቀም ላይ ያተኮረ ክትትል ማድረግን እንዲያካትት ተደርጓል፡፡ በሁለተኛው ምዕራፍ የአጠቃላይ ትምህርት ጥራት ማሻሻያ ፕሮግራም ማህበረሰቡ በት/ቤቶች ድጎማ በጀት አጠቃቀም ላይ ክትትል እንዲያደርግና በሂደቱ ተጠያቂነት እንዲኖር የሚያስችል የአሠራር ዘዴ (Social Accountability Mechanisms) እንዲኖር የሚፈቅድ ሲሆን የሚከተሉትን ጉዳዮች ያካትታል፡፡
    1. እያንዳንዱ ትምህርት ቤት ወይም አ.መ.ት. ማዕከል ለህዝብ በግልፅ የሚታይ ወይም ግልፅ በሆነ የት/ቤቱ ግቢ/አካባቢ የት/ቤቶች ድጎማ በጀት ማስታወቂያ ሰሌዳ ማዘጋጀት/ማቆም ይኖርበታል፡፡ ማህበረሰቡ ስለሚላከው ገንዘብ መጠንና አጠቃቀም በቂ ዕውቀት ኖሮት ተገቢውን ክትትል ለማድረግ እንዲችል ይረዳ ዘንድ የማስታወቂያ ሰሌዳው የት/ቤቶች ድጎማ በጀቱ መቼ እንደደረሰ፣ መጠኑ ምን ያል እንደሆነ፣ ለምን ተግባር መዋል እንዳለበት፣ እንዲሁም ዓመታዊ የሂሳብ ሪፖርት የሚያሳዩ በጉልህ ፊደሎች የተፃፉ መረጃዎች ማካተት/ማሳየት ይኖርበታል፡፡ ት/ቤቱ ወይም አ.መ.ት.ማ. ከሌሎች ምንጮች የተገኘ ገንዘብ ቢኖረውም የገንዘቡ ምንጭና ለምን ተግባር እንደዋለ የሚገልፅ ለብቻው በተለይ የተዘጋጀ ማስታወቂያ በት/ቤቶች ድጎማ በጀት የማስታወቂያ ሰሌዳ ላይ መለጠፍ ይኖርበታል፡፡
    2. የት/ቤቶች ድጎማ በጀት መመዝገቢያ ደብተር (School Grants Cash Book) እና ተዛማጅ ሰነዶች (ደረሰኞች፣ ለክፍያ የተዘጋጁ ቫውቸሮች፣ ወዘተ...) በአግባቡ ተደራጅተው በእያንዳንዱ ት/ቤትና አ.መ.ት.ማ. መቀመጥ ይኖርባቸዋል፡፡ እነዚህ ሰነዶች በማንኛውም ጊዜ ለወ.ተ.መ.ህ.፣ ለት/ቤቱ ማህበረሰብ፣ ለኢንስፔክተሮችና ለኦዲተሮች ክፍት መሆን አለባቸው፡፡
- የሁለተኛው ምዕራፍ የአጠቃላይ ትምህርት ጥራት ማሻሻያ ፕሮግራም ስድስተኛው መርሀ ግብር ንዑስ መርሀ ግብር የሆነው የፕሮጀክቱ ከሙኒኬሽን ጉዳዮች (Sub Component 6.2. communications Affairs) ተግባሮችም የፕሮጀክቱን አተገባበርና

ፍፃሜዎች/የተገኙ ውጤቶች በተለያዩ የመገናኛ ብዙሀን ዘዴዎች ለህዝብ ማሳወቅን ያካትታል፡፡ በዚህ መሠረት ይህንን ንዑስ መርሀ ግብር እንዲተገብር ሀላፊነት የተሰጠው የትምህርት ሚኒስቴር ኮሙኒኬሽን ጉዳዮች ዳይሬክቶሬት ተሻሽሎ የተዘጋጀው የት/ቤቶች ድጎማ በጀት እና የት/ቤት መሻሻል ዕቅድ ዝግጅት መመሪያዎችን ዋና ዋና ሃሳቦች/ይዘቶች በመጭመቅ በሬድዮ፣ በህትመት እና በኤለክትሮኒክ ሚዲያዎች ለህዝብ እንዲደርሱ ያደርጋል፡፡ ይህ ሁኔታ ሁሉም ባለድርሻ አካላት በፕሮጀክቱ ትኩረት ስለተሰጣቸው እጅግ አስፈላጊ የሆኑ የትምህርት ቤት ድጎማ በጀት ዝርዝር ጉዳዮች በቂ መረጃ እንዲኖራቸውና በትግበራው ሂደት እያንዳንዳቸው ሊያበረክቱዋቸው የሚችሉ አስተዋፅኦዎች/ድጋፎች በጉልህ ለማስቀመጥና ለማረጋገጥ ያስችላል፡፡

ክፍል 2፡ በፌደራል ደረጃ የሚሠራባቸው መመሪያዎች

2.1. የፌደራል ኃላፊነት

- በፌደራል ደረጃ የት/ቤቶች ድጎማ በጀት ፕሮግራም ስኬታማ እንዲሆን የማድረጉ ኃላፊነት በትምህርት ሚኒስቴር (ት.ሚ) ሥር የሚተዳደረው የዕቅድ ዝግጅትና ሀብት ማፈላለግ ዳይሬክቶሬት (ዕ.ዝ.ሀ.ማ.ዳ.) ይሆናል፡፡ ይህንን እውን ለማድረግም ዳይሬክቶሬቱ ከሌሎች ዳይሬክቶሬቶች ጋር በተለይም ከትምህርት ቤት መሻሻል መርሀ ግብር፣ ከአጠቃላይ ትምህርት ኢንስፔክሽን፣ ከመምህራንና የትምህርት አመራር ልማት፣ ከአፍ መፍቻና እንግሊዝኛ ትምህርት ልማት፣ ከመምህራንና የትምህርት ተቋማት የሙያ ፍቃድ አሰጣጥና እድሳት እና ከኮሙኒኬሽን ጉዳዮች ዳይሬክቶሬቶች ጋር እንዲሁም ከሂሳብና ሳይንስ ትምህርቶች ማሻሻያ ማዕከል ጋር በቅርብ በመተባበር ይሠራል፡፡
- የዕቅድ ዝግጅትና ሀብት ማፈላለግ ዳይሬክቶሬት (ዕ.ዝ.ሀ.ማ.ዳ.)፣ የትምህርት ቤት መሻሻል መርሀ ግብር ዳይሬክቶሬት እና የኮሙኒኬሽን ጉዳዮች ዳይሬክቶሬት የሚከተሉትን ተግባራት በመተባበር የማከናወን ሀላፊነት አለባቸው።
    - ***ተግባር*** 1: ተሻሽሎ የተዘጋጀውን የት/ቤቶች ድጎማ በጀት መመሪያ መተርጎምና ለሚመለከታቸው ተቋማት ማሰራጨት፡፡
    - ***ተግባር*** 2: የት/ቤቶች ድጎማ በጀት በማስመልከት ዓውደ ጥናቶችን ማዘጋጀት፣ ስልጠናዎችን መስጠትና ማስተባበር
    - ***ተግባር*** 3: የት/ቤቶች ድጎማ በጀትን በመደልደል ለሚመለከታቸው ክልሎች በወቅቱ እንዲላክ ማድረግና አፈፃፀሙን ማስተባበር፡፡
    - ***ተግባር*** 4: የት/ቤቶች ድጎማ በጀት አጠቃቀምን በተመለከተ ጥናቶች/ግምገማዎች ማካሄድ/ማስተባበርና በግኝቶቹ ላይ የተመሠረቱ ዓውደጥናቶችን ማካሄድ፡፡
    - ***ተግባር*** *5:* ብሄራዊ (ሀገራዊ) የኮሙኒኬሽን ፕሮግራም/መድረክ መተግበር፡፡

ተግባር 1: ተሻሽሎ የተዘጋጀውን የት/ቤቶች ድጎማ በጀት መመሪያ መተርጎምና ለሁሉም ክልሎች፣ ዞኖች፣ ወረዳዎች፣ ት/ቤቶችና አ.መ.ት.ማ. በየደረጃው በሚካሄዱ የስልጠና ዓውደ ጥናቶች አማካኝነት ማሰራጨት

ደረጃ	የሚላከው የት/ቤት ድጎማ አመዳደብ መመሪያ መጠን
ፌደራል	ለአገሪቱ የመጠባበቂያ አቅርቦት የሚሆን 500 ቅጂዎች
ክልል	ለእያንዳንዱ የክልል ት/ቢሮ 50 ቅጂዎች
ዞን	ለእያንዳንዱ የዞን ትምህርት ጽ/ቤት 10 ቅጂዎች
ወረዳ	ለእያንዳንዱ የወረዳ ትምህርት ጽ/ቤት 10 ቅጂዎች
ት/ቤችና አ.መ.ት ማዕከላት	ለእያንዳንዱ ት/ቤትና አ.መ.ት ማዕከል 5 ቅጂዎች

ተግባር 1 በተሳካ ሁኔታ መተግበሩን የሚያሳይ የውጤት መለኪያ	(1) የት/ቤቶች ድጎማ በጀት ተሻሽሎ ተዘጋጅቷል፡፡ በሁሉም እርከኖች ለሚገኙ የሚመለከታቸው ተቋማት ተዳርሷል፡፡

ተግባር 2፡ በት/ቤት የድጎማ በጀት አጠቃቀም መመሪያ ላይ ለክልል አሰልጣኞች የስልጠና ወርክሾፕ ማደራጀት

- የዕቅድ ዝግጅትና ሀብት ማፈላለግ ዳይሬክቶሬት (ዕ.ዝ.ሀ.ማ.ዳ.) እና የትምህርት ቤት መሻሻል መርሀ ግብር ዳይሬክቶሬት 100 ለሚያክሉ የክልል የት/ቤቶች የድጎማ በጀት መመሪያ አሰልጣኞች የሶስት ቀን የአሰልጣኞች ስልጠና ወርክሾፕ በማዘጋጀት ስልጠና ይሰጣሉ፡፡
- ከላይ የተጠቀሰው የአሰልጣኞች ስልጠና ከእያንዳንዱ ክልል የትም/ቢሮና የፋይናንስና ኢኮኖሚ ልማት ቢሮ ተሳታፊዎች ማካተት ይኖርበታል፡፡
- የትምህርት ቤቶች ድጎማ ፕሮግራም የፋይናንስ አስተዳደር/አሠራር ጉዳዮችን በተመለከተ ማብራሪያና ድጋፍ ለመስጠት እንዲቻል የክልል ፋይናንስና ኢኮኖሚ ልማት ቢሮዎች/ተወካዮች በክልል የአሰልጣኞች ስልጠና መገኘት ይኖርባቸዋል፡፡
- የክልል አሰልጣኞች ስልጠና ወርክሾ የሚከተሉትን ጉዳዮች ማካተት ይኖርበታል፡-

1. የትምህርት ቤት ድጎማ በጀት አመዳደብ መመሪያና በሁለተኛው ምዕራፍ የአጠቃላይ ትምህርት ጥራት ማሻሻያ ፕሮግራም ላይ መረጃን መሠረት ያደረገ የት/ቤት መሻሻል ዕቅድ ዝግጅት እንዲሁም ቢያንስ 50% የትም/ቤቶች ድጎማ በጀት በት/ቤት መሻሻል ዕቅድ ለመማር ማስተማር ርዕሰጉዳይ /domain/ እንዲውል የተደረገው የአቅጣጫ ለውጥ፡፡
2. የክልል ሠራተኞች የት/ቤቶች ድጎማ በጀትና መመሪያ በተመለከተ ለዞንና ለወረዳ ሠራተኞች ብቃት ያለው ሥልጠና መስጠት የሚችሉበትን ውጤታማ ዘዴ መቀየስ፡፡
3. የወረዳ አሰልጣኞች የት/ቤቶች ድጎማ በጀት መመሪያውን በሚመለከት ለወ.ተ.መ.ሀ ተወካዮች እንዲሁም ለት/ቤትና አ.መ.ት ማዕከሎች ርዕሰ መምህራን ማሰልጠን የሚችሉበት ውጤታማ ዘዴ መቀየስ፡፡
4. ለእያንዳንዱ ክልል የሚያስፈልገውን በጀት ከግምት ውስጥ ያስገባ የክልል ስልጠና ፕሮግራሞች ረቂቅ ዕቅድ ማዘጋጀት፡፡

ተግባር 2 በተሳካ ሁኔታ መተግበሩን የሚያሳይ የውጤት መለኪያ	(1) የክልል የአሰልጣኞች ወርክሾፕ ተካሂዷል፡፡ የወርክሾፕ ሪፖርትና የተሳታፊዎች ዝርዝር ተዘጋጅቷል፡፡

ተግባር 3፡ ለት/ቤቶች የሚመደበውን የድጎማ በጀት ገንዘብ ለክልሎች የማስተላለፍ ሥራን ማስተባበር

- የዕ.ዝ.ሀ.ማ.ዳ. ከፋይናንስና ኢኮኖሚ ልማት ሚኒስቴር (ፋ.ኢ.ል.ሚ) ጋር በመተባበር ለክልሎች የሚላከውን በጀት በማስላት ለክልሎች ይልካል፡፡
- የሚላከው ገንዘብ የሚሰላው በፌደራል የትምህርት አመራር መረጃ ሥርዓት (ት.አ.መ.ሥ) በሚሰበሰበው መረጃ መሰረት ይሆናል፡፡ ለምሳሌ የ2008 ዓ.ም. የት/ቤቶች ድጎማ በጀት ድልድል የተሠራው ከዚሁ መረጃ ሥርዓት የተገኘውን የ2006 ዓ.ም. መረጃ መሠረት በማድረግ ነው፡፡
- ስሌቱ ለትም/ቤቶችና አ.መ.ት.ማ. የተፈቀደውን ተጨማሪ የድጎማ በጀት ከግምት ውስጥ ያስገባ እንዲሆን ያስፈልጋል፡፡
- ገንዘቡ እንደተላከ የዕ.ዝ.ሀ.ማ.ዳ. ከፋ.ኢ.ል.ሚ ጋር በመተባበር በጠቅላላ የተላከውን የገንዘብ መጠን እንዲሁም ለእያንዳንዱ ክልልና ወረዳ የሚከፋፈለውን የገንዘብ መጠን ለሁሉም ክፍሎች በጽሁፍ ያሳውቃል፡፡

ተግባር 3 በተሳካ ሁኔታ መተግበሩን የሚያሳይ የውጤት መለኪያ	(1) በት.ሚ እና በፋ.ኢ.ል.ሚ የሚቀመጡ ለክልሎች የተላከውን ጠቅላላ የገንዘብ መጠን እንዲሁም ለእያንዳንዱ ክልልና ወረዳ የሚከፋፈለውን የገንዘብ መጠን የሚያሳዩ ደብዳቤዎች ቅጂዎች መኖር፡፡ (2) 80% የሚደርሱ ት/ቤቶችና አ.መ.ት.ማ. በየዓመቱ እ.ኤ.አ. ኦክቶበር 31 ላይ የድጎማ በጀታቸውን አግኝተዋል፡፡

ተግባር 4፡ የትምህርት ቤቶች የድጎማ በጀት አጠቃቀም ጥናቶችን/ግምገማዎችን ማካሄድና በግኝቶቹ ላይ የተመሠረቱ ዓውደጥናቶች ማካሄድ

- የዕ.ዝ.ሀ.ማ.ዳ. ከት/ቤት መሻሻል መርሀ ግብር ዳይሬክቶሬት ጋር በመተባበር የአገር ውስጥና ዓለም አቀፍ አማካሪዎች የሚገኙበት የአማካሪዎች ቡድን በመቅጠር/በማስቀጠር በአገሪቱ ውስጥ ከሚገኙት የአንደኛና ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች እንዲሁም አ.መ.ት ማዕከላት ውስጥ ናሙና በመውሰድ በት/ቤት የድጎማ በጀት ፕሮግራም አፈጻጸም ላይ ሁለት ጊዜ መደበኛ ጥናቶች/ግምገማዎች እንዲካሄዱ ያደርጋል፡፡
- የመጀመሪያው ጥናት/ግምገማ በፕሮጀክቱ ትግበራ የመጀመሪያ ዓመት ገደማ የሚካሄድ ሲሆን ሁለተኛው ጥናት በፕሮጀክቱ 3ኛ ዓመት የትግበራ ወቅት ይካሄዳል፡፡
- ለግምገማው/ለጥናቱ የሚያስፈልጉ ቢጋሮች ጥናቶቹ ከመጀመራቸው በፊት ተዘጋጅተው እንዲገመገሙ ይደረጋል፡፡ የቢጋሮቹ ግምገማ በትምህርት ቤቶች

ድጎማ ፕሮግራም አተገባበር የእያንዳንዱ እርከን ሚናዎችና የሚጠበቁ ውጤቶች መካተታቸውን ከግምት ውስጥ ያስገባል፡፡ ጥናቱ በወረዳ፣ በት/ቤቶች፣ በአ.መ.ት.ማ. እና በማህበረሰብ ደረጃ የፕሮግራሙ አፈፃፀም ረገድ ልዩ ትኩረት ያደርጋል፡፡

- ሁለተኛውጥናት/ግምገማ መደበኛ የፕሮግራሙ ግምገማ ከተጠናቀቀ በኋላ የፕሮግራሙን አጠቃላይ የአፈፃፀም ገፅታ ለመገምገም/ለመረዳት እንዲቻል የትምህርት ቤት መሻሻል ፕሮግራም ዳይሬክቶሬት ከዕቅድ ዝግጅትና ሀብት ማፈላለግ ዳይሬክቶሬት ጋር በመተባበር ከፋይናንስና ኢኮኖሚ ልማት ሚኒስቴር፣ ከክልል ት/ቢሮዎች፣ ከክልል ፋይናንስና ኢኮኖሚ ልማት ቢሮዎች፣ ከናሙና ወረዳዎች፣ ት/ቤቶችና አ.መ.ት.ማ. የተወጣጡ ተሳታፊዎች የሚገኙበት የሁለት ቀናት ዓውደ ጥናት ያካሂዳል፡፡

ተግባር 4 በተሳካ ሁኔታ መተግበሩን የሚያሳይ የውጤት መለኪያ	(1) በሁለተኛው ምዕራፍ የአጠቃላይ ትምህርት ጥራት ማሻሻያ ፕሮጀክት ወቅት የሚካሄደው የመጀመሪያው የትምህርት ቤቶች ድጎማ በጀት አጠቃቀም ጥናት/ግምገማ ሪፖርት ለትምህርት ሚኒስቴር ቀርቧል፡፡ (2) በሁለተኛው ምዕራፍ የአጠቃላይ ትምህርት ጥራት ማሻሻያ ፕሮጀክት ወቅት የሚካሄደው ሁለተኛውና የመጨረሻው የትምህርት ቤቶች ድጎማ በጀት አጠቃቀም ጥናት/ግምገማ ሪፖርት ለትምህርት ሚኒስቴር ቀርቧል፡፡ (3) ዓውደ ጥናት ተካሂዶ የተሳታፊዎችን ዝርዝር ያካተተ ሪፖርት ተዘጋጅቷል፡፡

ተግባር 5፡ ብሄራዊ (ሀገራዊ) የኮሙኒኬሽን ፕሮግራም/መድረክ ማመቻቸትና መተግበር፡፡

1. የትምህርት ሚኒስቴር ኮሙኒኬሽን ጉዳዮች ዳይሬክቶሬት ከት/ቤት መሻሻል መርሀ ግብር እና ዕ.ዝ.ሀ.ማ.ዳ. ዳይሬክቶሬቶች ጋር በመተባበር ሀገራዊ የኮሙኒኬሽን መድረክ በማመቻቸት/በመንደፍ ይተገብራል፡፡ ዳይረክቶሬቱ ይህንን ተግባር በወቅቱና በጥራት የመፈፀም ሃላፊነት አለበት፡፡

- የኮሙኒኬሽን ጉዳዮች ዳይሬክቶሬት ስለ ሁለተኛው ምዕራፍ የአጠቃላይ ትምህርት ጥራት ማሻሻያ ፕሮግራም የትኩረት አቅጣጫ ለውጥ (ማለትም መረጃን መሠረት ያደረገ የት/ቤት መሻሻል ዕቅድ ዝግጅትና ከት/ቤቶች ድጎማ በጀት ቢያንስ 50% ለመማር ማስተማር ርዕሰ ጉዳይ/domain/ መዋል ስላለበት ፣ ስለ ት/ቤቶች ድጎማ በጀት አፈፃፀም ዝርዝርና ሌሎች ጠቃሚ ጉዳዮችን የሚመለከቱ መልዕክቶችን ማቅረብ ይጠበቅበታል፡፡

- በተለያዩ ሚዲያዎች የሚሰራጨው መልዕክት በሁሉም ክልሎች በሚገኙት ማህበረሰቦች፣ ት/ቤቶችና አ.መ.ት.ማ. ዘንድ መድረስ ይኖርበታል፡፡

ተግባር 5 በተሳካ ሁኔታ መተግበሩን የሚያሳይ የውጤት መለኪያ	(1) የትምህርት ቤት መሻሻል ዕቅድ አተገባበር፣ የትምህርት ቤቶች ድጎማ በጀት አጠቃቀም፣ የወላጆች፣ የወ.ተ.መ.ህ. ሚናና ሃላፊነት እንደዚሁም ማህበረሰቡ የድጎማ በጀት አጠቃቀምን ለመከታተል የሚያስችሉት የተጠያቂነት መርሆዎችን ያካተቱ የድምፅና የቪድዮ መልእክቶች/ስክሪፕቶች ተዛጋጅተው ሁሉምየማህበረሰብ ክፍሎችና ክልሎች እንዲያውቁዋቸው ተደርጓል፡፡

ክፍል 3፡ በክልል ደረጃ የሚሠራባቸው መመሪያዎች

3.1. የክልሎች ኃላፊነት

- የክልል የትምህርት ቢሮዎች (ክ.ትም.ቢ.) እና የፋይናስና ኢኮኖሚ ልማት ቢሮዎች (ፋ.ኢ.ል.ቢ) በእያንዳንዱ ክልል ውስጥ የት/ቤት የድጎማ በጀት ፕሮግራም ስኬታማ እንዲሆን የማድረግ ኃላፊነት አለባቸው፡፡ የክ.ትም.ቢ እና የፋ.ኢ.ል.በ የሚከተሉት ተግባራት ይኖሩዋቸዋል፡፡
    - *ተግባር 1:* የት/ቤቶች ድጎማ በጀት መመሪያን በሚመለከት በዞን እና በወረዳ ደረጃ የሥልጠና ወርክሾፖችን ማደራጀት/ማካሄድ፡፡
    - *ተግባር 2:* ወረዳዎች ልዩ ፍላጎት ላላቸው ተማሪዎች የሚያስፈልጉ የትምህርት መሣሪያዎችን በማሟላት ድጋፍ ማድረግ እንዲችሉ ተብሉ የተመደበውን ተጨማሪ የትምህርት ቤቶች ድጎማ በጀት እንዲደርሳቸው ማድረግ፡፡
    - *ተግባር 3:* የትምህርት ቤቶች ድጎማ በጀት የስርጭት/የድልድል ደብዳቤዎች በወቅቱ ለሚመለከታቸው ሁሉም ወረዳዎች እንዲደርሱ ማድረግ፡፡
    - *ተግባር 4:* የት/ቤቶች የድጎማ በጀት ፕሮግራም ክትትልና ግምገማ ማካሄድ/መቆጣጠር

የዞን ትምህርት ጽ/ቤቶች በሌሉባቸው ክልሎች የክልል ትም/ቢሮዎች የዞን ትም/ጽ/ቤቶችን ተግባራት/ሃላፊነቶች ተክተው ይሠራሉ፡፡ (ገፅ 22 ይመልከቱ)

ተግባር 1፡ የት/ቤት የድጎማ በጀት መመሪያን በሚመለከት በዞን እና በወረዳ ደረጃ የሥልጠና ወርክሾፖችን ማደራጀት/ማካሄድ

- በፌደራል ደረጃ በሚካሄደው የሶስት ቀን የክልሎች ወርክሾፕ ላይ የተገኙት የክ.ትም.ቢ እና የፋ.ኢ.ል.ቢሮ ባለሙያዎች በክልል ደረጃ የአንድ ቀን የስልጠና ወርክሾፕ ማዘጋጀት ያለባቸው ሲሆን በስልጠናው የሚከተሉት አካላት ይሳተፋሉ፡-
    - ከእያንዳንዱ የወረዳ ትምህርት ጽ/ቤት የጽ/ቤቱ ሃላፊ፤
    - ከእያንዳንዱ የወረዳ ትምህርት ጽ/ቤት፤ የጽ/ቤቱ የዕቅድ ዝግጅት ክፍል ሃላፊ/ባለሙያ፤

- ከእያንዳንዱ ወረዳ አንድ የወረዳ ፋይናንስና ኢኮኖሚ ልማት ጽ/ቤት ባለሙያ፤
- ከእያንዳንዱ ዞን ሁለት የዞን ትምህርት ጽ/ቤት ባለሙያዎች (አንድ ሃላፊና አንድ ባለሙያ)፡፡

- በእያንዳንዱ ወርክሾፕ ላይ የሚካፈሉት ሰልጣኞች ቁጥር ከ50 መብለጥ የሌለበት ሲሆን በየክልሉ የሚካሄዱ ወርክሾፖች ብዛት እንደ ክልሉ ስፋት/ተጨባጭ ሁኔታ ይወሰናል፡፡
- የስልጠናው ወርክሾፕ የሚከተሉትን ተግባራት ያካትታል፡-
  - በትምህርት ቤቶች የድጎማ በጀት መመሪያ ላይ ተገቢውን ግንዛቤ ማስጨበጥ፡፡ በዚህ ክፍል በሁለተኛው ምዕራፍ የአጠቃላይ ትምህርት ጥራት ማሻሻያ ፕሮግራም ላይ የተደረገው የትኩረት አቅጣጫ ለውጥ፣ ማለትም መረጃን መሠረት ያደረገ የት/ቤት መሻሻል ዕቅድ ዝግጅት እንዲሁም ቢያንስ 50% የትም/ቤቶች ድጎማ በጀት በት/ቤት መሻሻል ዕቅድ ለመማር ማስተማር ርዕሰ ጉዳይ /domain/ እንዲውል የተደረገው የአቅጣጫ ለውጥ መካተት ይኖርበታል፡፡
  - የወ.ተ.መ.ህ. ተወካዮች፣ የትም/ቤቶችና የአ.መ.ት.ማ. ርዕሰ መምህራን በት/ቤቶች ድጎማ ፕሮግራም አተገባበር የሚኖሩዋቸው ሚናዎችና ሊያበረክቱዋቸው የሚችሉ እስተዋፅኦዎች ያካተተ አዋጪ የስልጠና ዘዴን መለየትና መጠቀም ያስፈልጋል፡፡

ተግባር 1 በተሳካ ሁኔታ መተግበሩን የሚያሳይ የውጤት መለኪያ	(1) የዞንና የወረዳ የሥልጠና ወርክሾፕ ሪፖርትና የተሳታፊዎች ዝርዝር ለትምህርት ሚኒስቴር/ለፕሮጀክቱ ጽ/ቤት ቀርቧል፡፡

ተግባር 2: ወረዳዎች ልዩ ፍላጎት ላላቸው ተማሪዎች የሚያስፈልጉ የትምህርት መሣሪያዎችን በማሟላት ድጋፍ ማድረግ እንዲችሉ ተብሉ የተመደበውን ተጨማሪ የትምህርት ቤቶች ድጎማ በጀት እንዲደርሳቸው ማድረግ፡፡

- የክልል ትምህርት ቢሮዎች (ክ.ት.ቢ.) እና የፋይናንስና ኢኮኖሚ ልማት ቢሮዎች (ፋ.ኢ.ል.ቢ) በትምህርት ሚኒስቴር የተመደበውን የት/ቤቶች ድጎማ በጀት መጠን ትክክለኛነት ያረጋግጣሉ፡፡
- የክልል ትምህርት ቢሮዎች ልዩ ፍላጎት ላላቸው ተማሪዎች ትምህርት ማጠናከሪያ የተላከው 1% ተጨማሪ የት/ቤቶች ድጎማ ተማሪዎቹ የሚገኙባቸውን ወረዳዎችና

ት/ቤቶች ባላቸው ዕውቀት/መረጃ መሠረት በመለየት ገንዘቡ ደርሶ በተገቢው ሥራ ላይ እንዲውል ማድረግ፡፡

- ልዩ ፍላጎት ያላቸው ተማሪዎች ያሉዋቸው ወረዳዎች ከሌሎች ወረዳዎች በተለየ ሁኔታ ልዩ ትኩረትና ድጋፍ ይደረግላቸዋል፡፡ በተመሳሳይ መንገድ ወረዳዎቹ ለዚሁ ጉዳይ የተመደበው የድጎማ በጀት የተመዘገቡ ልዩ የትምህርት ፍላጎት ያላቸው ተማሪዎችን ብዛት መሠረት በማድረግ ተማሪዎቹ ለሚገኙባቸው ት/ቤቶች መላክ ይኖርባቸዋል፡፡
- ከዚህ በተጨማሪ የክልል ትምህርት ቢሮዎች አካታች የሆነ የትምህርት አሰጣጥ ስርዓት ለማጠናከርና ልዩ ፍላጎት ላላቸው ተማሪዎች የሚያስፈልጉ የትምህርት መሣሪያዎች አቅርቦትን ለማሻሻል በሚረዳ መልኩ ገንዘቡን ለሁሉም ወረዳዎች የማዳረስ ነፃነት/መብት አላቸው፡፡
- የክልል ትምህርት ቢሮዎች ልዩ ፍላጎት ላላቸው ተማሪዎች የሚመደበው ተጨማሪ ገንዘብ ለምን ተግባር ማዋል እንደሚገባ ከወሰኑ በኋላ ገንዘቡ ለእያንዳንዱ ወረዳ የተደለደለበት አሠራር፣ ተግባርና የገንዘብ መጠን መረጃ/ሰነዶች አደራጅተው ማስቀመጥ ይገባቸዋል፡፡

ተግባር 2 በተሳካ ሁኔታ መተግበሩን የሚያሳይ የውጤት መለኪያ	(1) የክልል ትምህርት እና የፋይናንስና ኢኮኖሚ ልማት ቢሮዎች ልዩ ፍላጎት ላላቸው ህፃናት የተመደበውን ገንዘብ ወረዳዎች ዘንድ በወቅቱ መድረሱን የሚያረጋግጥ ሰነድ አደራጅተው ይዘዋል፡፡

ተግባር 3: የትምህርት ቤቶች ድጎማ በጀት የስርጭት/የድልድል ደብዳቤዎች በወቅቱ ለሚመለከታቸው ሁሉም ወረዳዎች እንዲደርሱ ማድረግ፡፡

- የክ.ት.ቢ. እና የክ.ፋ.ኢ.ል.ቢ. ከትምህርት ሚኒስቴር የተላከውን ጠቅላላ የት/ቤቶች ድጎማ በጀት ትክክለኛነት ያረጋግጣሉ፡፡
- የክ.ት.ቢ. በየወረዳው ለሚገኙ ት/ቤቶችና የአ.መ.ት.ማ. የተላከውን የት/ቤቶች ድጎማ በጀት ዝርዝር የሚገልፁ ደበዳቤዎች በማዘጋጀት ለእያንዳንዱ ወረዳ እንዲደርሱ ያደርጋል፡፡
- የክ.ት.ቢ. ለእያንዳንዱ ወረዳ መደበኛ ደብዳቤ ሲልክ የሚደርሳቸውን የት/ቤት ድጎማ በጀት መጠን የት/ቤቶች እና አ.መ.ት ማዕካላት ዝርዝርና ለእያንዳንዱ

የትምህርት ተቋም የተመደበውን የገንዘብ መጠን ያሳውቃል፡፡ በእያንዳንዱ ደብዳቤ ላይ ከታች የተመለከተው ሰንጠረዥ ቁጥር 5 ተሟልቶ መስፈር ይኖርበታል፡፡

ሰንጠረዥ 5. በእያዳንዱ ወረዳ ለሚገኙ ት/ቤቶችና አ.መ.ት.ማ. የተመደበ የትምህርት ቤቶች የድጎማ በጀት ክፍፍል

የወረዳው ስም፡			
የት/ቤቱ እርከን (ደረጃ)	የተማሪዎች ብዛት	ለአንድ ተማሪ የተመደበው ዝቅተኛ በጀት (ብር)	ለወረዳው የተመደበ ጠቅላላ የገንዘብ መጠን (ብር)
ከ1-4 ክፍል		50	
ከ5-8 ክፍል		55	
አ.መ.ት ማዕከል		50	
ከ9-10 ክፍል		60	
ከ11-12 ክፍል		70	
ድምር		----------	
በየወረዳው ለሚገኙ ከ200 ተማሪዎች በታች ያሉዋቸው ት/ቤቶች የተመደበ ተጨማሪ የድጎማ በጀት			
በየወረዳው ለሚገኙ ልዩ ፍላጎት ያላቸው ተማሪዎች ላሉዋቸው ት/ቤቶች የተመደበ 1% ተጨማሪ የድጎማ በጀት			
ጠቅላላ ድምር			

- ለወረዳ የሚላክ ደብዳቤ በግልባጭ ለዞን የትምህርት ጽ/ቤትም መላክ ይኖርበታል፡፡ ደብዳቤው ገንዘቡ ወደ ወረዳዎች የባንክ ሒሳብ ከመዛወሩ በፊት መላክ ያለበት ሲሆን ይህም ወረዳዎች በባንክ ሂሳባቸው ውስጥ ገቢ የሚደረገውን የገንዘብ መጠን ለማወቅ ያስችላል፡፡
- እንዲሁም ደብዳቤው ወረዳዎች በፌደራል ደረጃ (ፌደራል የት.አ.መ.ሥ የተሰበሰበውን መረጃ በመጠቀም) የተሰላውን ዝቅተኛ የበጀት መጠን መሰረት በማድረግ ሙሉዉን የትምህርት ቤት በጀት ለት/ቤቶችና አ.መ.ት ማዕከላት ማከፋፈል እንደሚኖርባቸው የሚገለጽ መሆን አለበት፡፡
- የክ.ት.ቢ ከፋ.አ..ል.ቢ.. ጋር በመተባበር ለወረዳዎች በተላከው ደብዳቤ ላይ በሰፈረው መሰረት ለወረዳዎች ገንዘብ ይልካል፡፡ ገንዘብ እንደተላከ የክ.ት.ቢ ለወረዳዎች ያሳውቃል፡፡

ተግባር 3 በተሳካ ሁኔታ መተግበሩን የሚያሳይ የውጤት መለኪያ	(1) *ለወረዳዎች እንዲሁም በየወረዳው ለት/ቤቶችና አ.መ.ት.ማ. የተላከውን የገንዘብ መጠን የሚያሳዩ ሰነዶች በክ.ት.ቢ. እና በፋ.አ..ል.ቢሮ መገኘት፡፡* (2) *ለወረዳ የተላኩ በጀቶች የሚያሳይ ሰነድ በፋ.አ..ል.ቢሮ መገኘት፡፡*

ተግባር 4፡ የት/ቤቶች የድጎማ በጀት ፕሮግራም ክትትልና ግምገማ ማካሄድ/መቆጣጠር

- የክ.ት.ቢ. ከፋ.ኢ.ል.ቢ ሠራተኞች ጋር በመሆን ወረዳዎችን ለመጎብኘት እቅድ ማውጣት አለባቸው፡፡ የዚህ ጉብኝት ዓላማ (ሀ) ወረዳዎች ገንዘቡን በአግባቡ እንደተጠቀሙበትና ለትምህርት ቤቶችና አ.መ.ት ማዕከላት የተወሰወነውን ዝቅተኛ የድጎማ በጀት መጠን መላካቸውን ለማረጋገጥ እና (ለ) ትምህርት ቤቶችና አ.መ.ት ማዕከላት ገንዘቡ እንደደረሳቸውና በአግባቡ እንደተጠቀሙበት ለማረጋገጥ ነው፡፡
- በዚህ ሂደት በአባሪ 3 ላይ የቀረበውን የት/ቤቶች ድጎማ በጀት መመዝገቢያ ቅፅ በልዩ ትኩረት ማየት/መመርመር ያስፈልጋል፡፡

ተግባር 4 በተሳካ ሁኔታ መተግበሩን የሚያሳይ የውጤት መለኪያ	(1) የወረዳ/ትምህርት ቤቶች/አ.ት.መ.ማ. ጉብኝት መቆጣጠሪያ ሪፖርትና እንደ አስፈላጊነቱ የተወሰደ እርምት ማስታወሻ በክ.ት.ቢ. መገኘት፡፡

ክፍል 4፡ በዞን ደረጃ የሚሠራባቸው መመሪያዎች

4.1. የዞን ኃላፊነት

- ዞኖች ጠቃሚ የትምህርት መዋቅሩ ክፍል እንደመሆናቸው መጠን የዞን የትምህርት ጽ/ቤቶች (ዞ.ት.ጽ.ቤ) ለወረዳዎች የክትትልና የማማከር አገልግሎት የመስጠት ኃላፊነት ይኖራቸዋል፡፡ የዞ.ት.ጽ.ቤ. የሚከተሉት ሁለት ኃላፊነቶች ይኖሩታል፡፡
  - **ተግባር 1**: *የወረዳ የት/ቤት ድጎማ በጀት ስልጠና ወርክሾፖችን በበላይነት ማስተባበር*
  - **ተግባር 2**: *የትምህርት ቤት የድጎማ በጀት ፕሮግራሙን መከታተል*

የዞን ትምህርት ጽ/ቤቶች በሌሉባቸው ክልሎች የክልል ትም/ቢሮዎች የዞን ትም/ጽ/ቤቶችን ተግባራት/ሃላፊነቶች ተክተው ይሠራሉ፡፡

ተግባር 1፡ የወረዳ የት/ቤት የድጎማ በጀት ስልጠና ወርክሾፖችን በበላይነት ማስተባበር

- የዞ.ት.ጽ.ቤ. ሠራተኞች የወረዳ ትምህርት ጽ/ቤት (ወ.ት.ጽ.ቤ..) ሠራተኞችና የወረዳ የፋይናንስና የኢኮኖሚ ልማት ጽ/ቤት (ወ.ፋ.ኢ.ል.ጽ.ቤ.) ሠራተኞች በወረዳው ውስጥ ካሉት ከእያንዳንዱ የመጀመሪያና ሁለተኛ ደረጃ ት/ቤቶችና የአ.መ.ት ማዕከላት ለሚውጣጡ ሶስት ሰዎች የት/ቤት ድጎማ በጀት የሚመለከቱ የስልጠና ወርክሾፖችን በተሳካ ሁኔታ እንዲያዘጋጁ ድጋፍ ይሰጣሉ፡፡
- የወረዳው ሠራተኞች አቅም የሚያንሳቸው ከሆነ የዞ.ት.ጽ.ቤ. ሠራተኞች እንደ አስፈላጊነቱ በት/ቤት የድጎማ በጀት መመሪያው ላይ በተዘጋጀ ወርክሾፕ ላይ ስልጠና ሊሰጡ ይችላሉ፡፡

ተግባር 1 በተሳካ ሁኔታ መተግበሩን የሚያሳይ የውጤት መለኪያ	(1) በወረዳ ደረጃ የተካሄዱትን የት/ቤት ድጎማ በጀት መመሪያ ስልጠና ወርክሾፖችን በሚመለከት በዞን ሠራተኞች የቀረበ ሪፖርት መቅረብ፡፡

ተግባር 2፡ የትምህርት ቤት ድጎማ በጀት ፕሮግራሙን መከታተል

- የዞን ትምህርት ጽ/ቤት ሠራተኞች የድጎማ ገንዘብ አጠቃቀምን ለመቆጣጠር በሁሉም ወረዳዎች የሥራ ጉብኝት ያደርጋሉ፡፡ እየተዘዋወሩ ለተመሳሳይ ክትትል

ጉብኝት ለሚያደርጉት የክ.ት.ቢ. ሠራተኞችም ተገቢውን ድጋፍ ማድረግ አለባቸው፡፡ በክልል ትምህርት ቢሮዎች እንደሚሠራበት ሁሉ የዞን ት/ጽ/ቤት ሠራኞች አዲስ ከተዘረጋው የኢንስፔክሽን ስርዓት ጋር በመደጋገፍ ይሠራሉ፡፡

ተግባር 1 በተሳካ ሁኔታ መተግበሩን የሚያሳይ የውጤት መለኪያ	(1) በወረዳ ደረጃ የተካሄደውን የት/ቤት የድጎማ በጀት የክትትልና ግምገማ ሪፖርት በዞን ት.ጽ.ቤት. መገኘትና ለሚመለከተው የላይኛው እርከን እንዲተላለፍና ለፕሮጀክቱ ጽ/ቤት እንዲደርስ ማድረግ፡፡

ክፍል 5፡ በወረዳ ደረጃ የሚሰራባቸው መመሪያዎች

5.1. የወረዳ ኃላፊነት

- የወረዳው የትምህርት ጽ/ቤት (ወ.ት.ጽ/ቤ) እና የወረዳው የፋይናንስና ኢኮኖሚ ልማት ጽ/ቤት (ወ.ፋ.ኢ.ል.ቢ.) በእያንዳንዱ ወረዳ የት/ቤቶች ድጎማ በጀት ፕሮግራም በተሳካ ሁኔታ መከናወኑን የማረጋገጥ ኃላፊነት አለባቸው፡፡ በዚህ መሠረት የወ.ት.ጽ/ቤት እና የወፋ.ኢ.ል.ጽ/ቤት የሚከተሉት ኃላፊነቶች ይኖሩዋቸዋል፡፡
    - ***ተግባር 1:*** የወረዳ የት/ቤት ድጎማ በጀት ስልጠና ወርክሾፖችን ማደራጀትና ማስተባበር
    - ***ተግባር 2:*** ለትምህርት ቤቶችና የአ.መ.ት ማዕከላት የት/ቤት ድጎማ በጀት መመደብ
    - ***ተግባር 3:*** ልዩ ፍላጎት ላላቸው ተማሪዎች የተመደበ ተጨማሪ በጀት ጭምር (ካለ) ለት/ቤቶችና አ.መ.ት ማዕከላት የተመደበላቸውን የት/ቤቶች ድጎማ በጀት መጠን ማሳወቅ
    - ***ተግባር 4:*** ለትምህርት ቤቶችና የአ.መ.ት ማዕከላት የት/ቤት ድጎማ በጀት መስጠት
    - ***ተግባር 5:*** የት/ቤቶች ድጎማ በጀት ፕሮግራም አጠቃላይ ክትትል ማደረግ እንዲሁም ለት/ቤቶች እና አ.መ.ት. ማዕከላት ድጋፍ መስጠት

ተግባር 1፡ የወረዳ የት/ቤት የድጎማ በጀት ስልጠና ወርክሾፖችን ማደራጀትና ማስተባር

- በክልል ደረጃ ለአንድ ቀን በተካሄደ የት/ቤት ድጎማ በጀት ፕሮግራም ሥልጠና ወርክሾፕ ላይ የተገኙት የወረዳው ሠራተኞች በወረዳ ደረጃ ለወ.ተ.መ.ህ. አባላት፣ ለመጀመሪያና ሁለተኛ ደረጃ ት/ቤቶች ርዕሰ መምህራን እንዲሁም ለአ.መ.ት. ማዕከላት ተወካዮች የአንድ ቀን የት/ቤቶች ድጎማ በጀት ስልጠና ወርክሾፕ ማዘጋጀት ይኖርባቸዋል፡፡
- የወረዳ ትምህርት ጽ/ቤት ሠራተኞች ከእያንዳንዱ ት/ቤትና የአ.መ.ት. ማዕከል የተውጣጡ በስልጠናው ላይ የሚሳተፉ ሶስት ሰዎች ለይተው ይመድባሉ፡፡ የቀበሌ ትምህርትና ስልጠና ቦርድ በሚገኝባቸው አካባቢዎች ደግሞ እነዚህ አካላት በስልጠናው ላይ የሚሳተፉ ባለሙያዎችን በመለየት ረገድ ወረዳዎችን ያግዛሉ፡፡ የስልጠናው ተሳታፊዎች ምርጫ በሚከተሉት መስፈርቶች መሠረት ይፈፀማል፡፡
    - ከስልጠናው ተሳታፊዎች ውስጥ አንዱ የወ.ተ.መ.ህ. አባል መሆን አለበት፡፡

- ሁለተኛው ተሳታፊ የት/ቤት ወይም የአ.መ.ት. ማዕከል ርዕሰ መምህር ወይም ምክትል ርዕሰ መምህር መሆን ይኖርበታል፡፡
- ሦስተኛው ተሳታፊ ደግሞ ተጨማሪ የወ.ተ.መ.ህ. አባል ወይም በት/ቤቱ ወይም የአ.መ.ት.ማ. ጉልህ ተሳትፎ ያለው የማህበረሰብ አባል መሆን አለበት፡፡
- በስልጠናው ላይ የሚሳተፉ ሰዎች የትምህርት ቤቶች ድጎማ በጀት ፕሮግራምን በስኬት እንዲተገበር ጉልህ አስተዋፅኦ ማበርከት ስለሚገባቸው ለስልጠናው ሲመረጡ ጠንካራ ተሳታፊዎችን መምረጥ ያስፈልጋል፡፡

- የወርክሾፑ ዓላማ የት/ቤቶች ድጎማ በጀት አመዳደብ መመሪያዎችን ለማብራራትና ፕሮግራሙን በመተግበር ረገድ የእያንዳንዱን ባለድርሻ ሚናና ኃላፊነት ለመለየትና ለማስገንዘብ ነው፡፡
- ስልጠናው የሁለተኛው ምዕራፍ አጠቃላይ ትምህርት ጥራት ማሻሻያ ፕሮግራም የትኩረት አቅጣጫን (ማለትም በመረጃ ላይ የተመሠረተ የት/ቤት መሻሻል ዕቅድ ዝግጅት እና ቢያንስ 50% የት/ቤቶች ድጎማ በጀት ለመማር ማስተማር ርዕሰ ጉዳይ/domain/ መጠቀምን አበክሮ ማስገንዘብ ይኖርበታል፡፡
- በእያንዳንዱ የስልጠና ወርክሾፕ ላይ የሚካፈሉት ተሳታፊዎች ብዛት ከ50 መብለጥ የለበትም፡፡

ተግባር 1 በተሳካ ሁኔታ መተግበሩን የሚያሳይ የውጤት መለኪያ	(1) በወረዳ የት/ቤቶች ድጎማ በጀት ስልጠና ሪፖርትና የተሳታፊዎች ስም ዝርዝር በወረዳው መገኘት፡፡

ተግባር 2፡ ለትምህርት ቤቶችና የአ.መ.ት ማዕከላት የት/ቤት የድጎማ በጀት መመደብ

- የወረዳ ትምህርት ጽ/ቤት እና የወረዳ ፋ.ኢ.ል.ጽ.ቤት. ለወረዳው የት/ቤቶች ድጎማ በጀት መመደቡን የሚገልፅ ደብዳቤ ከክ.ት.ቢ. እንደደረሳቸው የጋራ ስብሰባ በማካሄድ በወረዳው ለሚገኙ ት/ቤቶች እና አ.መ.ት.ማ. የተመደበው የገንዘብ መጠን ትክክለኛነትን ያረጋግጣሉ፡፡
- የወ.ት.ጽ/ቤት እና የወ.ፋ.አ.ል/ጽቤት በጋራ የሚሰበሰቡበት ዓላማ፡-

- ለአ.መ.ት ማዕከላትና ትናንሽ ት/ቤቶች ለተማሪዎች በነፍስ ወከፍ ከተመደበው በጀት የበለጠ መጠን ከሌላ ምንጭ መስጠት የሚቻልበት መንገድ ካለ ለመወያየት፡
- ከክ.ት.ቢ. በወረዳው ለሚገኙ ልዩ ፍላጎት ላላቸው ተማሪዎች ት/ቤቶች ተብሎ የተላከ 1% ተጨማሪ የድጎማ በጀት ካለ ለሚመለከታቸው ት/ቤቶች ስለሚደርስበት መንገድ ለመወያየት፣
- ለት/ቤቶችና ለአ.መ.ት ማዕከላት የሚሰጠውን ጠቅላላ የት/ቤት ድጎማ በጀት መጠን ለማረጋገጥ፣

- የወ.ት.ጽ/ቤት የስብሰባውን ቃለ ጉባኤ መያዝ ያለበት ሲሆን ከዚያም የመጨረሻውን የስምምነት ውሳኔ በወ.ት.ጽ.ቤ. የት/ቤቶች ድጎማ በጀት መዝገብ ውስጥ እንዲቀመጥ ያደርጋል፡፡
- በስብሰባው ላይ ውይይት የሚደረግባቸው አጀንዳዎች የሚከተሉት ናቸው።

የስብሰባ አጀንዳ ቁጥር 1፡- ከ200 በታች ተማሪዎች ላሉዋቸው አነስተኛ ትምህርት ቤቶችና አ.መ.ት. ማዕከላት 200 ተማሪዎች እንዳሉዋቸው በመቁጠር የት/ቤቶች ድጎማ በጀት እንዲሰጣቸው መወሰን፡፡

- ከ200 ተማሪዎች በታች ላሉዋቸው ትንንሽ ት/ቤቶችና አ.መ.ት ማዕከላት 200 ተማሪዎች እንዳሉዋቸው ታሳቢ በማድረግ የት/ቤቶች ድጎማ በጀት ይመደብላቸዋል፡፡
- ይህ የሚደረግበት ምክንያት በፌደራል ደረጃ የተወሰነው ዝቅተኛ የነፍስ ወከፍ በጀት መጠን ከ200 ተማሪዎች በታች ላሉዋቸው አነስተኛ ትምህርት ቤቶችና የአ.መ.ት ማዕከላት ብዙ ሊጠቅማቸው የማይችል በመሆኑ ነው። ምክንያቱም የገንዘቡ መጠን በጣም ዝቅተኛ ስለሚሆን የትምህርት ቤቱን ብቃትና የትምህርት ጥራትን ለማሻሻል የተፈለገውን ያህል ላይሆን ይችላል፡፡ አብዛኛውን ጊዜ አ.መ.ት ማዕከላትና አነስተኛ ትምህርት ቤቶች የሚገኙት በኢኮሚ ዝቅተኛ በሆኑና ብዙ አገልግሎቶች በሌሎባቸው የገጠር አካባቢዎች ስለሆነ የትምህርት ጥራትን ለማሻሻል እንዲችሉ ሻል ያለ የት/ቤት በጀት ቢሰጣቸው ጠቃሚ ነው፡፡ ከዚህ በተጨማሪ አ.መ.ት ማዕከላትና አነስተኛ የተማሪ ቁጥር ያላቸው ት/ቤቶች እንደ ‹‹ትምህርት ለሁሉም›› የመሳሰሉትን ብሔራዊ የትምህርት ግቦችና አለማቀፋዊ ስምምነቶች

በማሳከት ረገድ እንዲሁም የሴት ተማሪዎች ቁጥርን በመጨመርና በትምህርቱ ዘርፍ የፆታ እኩልነትን በማረጋገጥ ረገድ ጉልህ አዎንታዊ ሚና ይጫወታሉ፡፡

- የወ.ት.ጽ/ቤት እና ወ.ፋ.ኢ.ል.ጽ/ቤት ሃላፊዎች በወረዳው ከሚገኙ ት/ቤቶችና አ.መ.ት.ማ. ውስጥ ከ200 ተማሪዎች በታች ያሉዋቸውን ለይተው በማውጣት 200 ተማሪዎች እንዳሉዋቸው በመቁጠር/ታሳቢ በማድረግ የድጎማ በጀቱን ይመድቡላቸዋል፡፡ በዚህ መሠረት ዝቅተኛው የሚመደበው ገንዘብ ለአ.መ/ት. ማዕከላት ብር 10,000.00፤ ለመጀመሪያ ደረጃ 10,000.00፤ እና ለሁለተኛ ደረጃ 12,000.00 ይሆናል ማለት ነው፡፡
- ለወረዳዎች የሚላከው የት/ቤቶች ድጎማ በጀት ምደባ ደብዳቤ ከ200 ተማሪዎች በታች እንዳሉዋቸው ተለይተው ለተቀመጡ ት/ቤቶችና አ.መ.ት.ማ. ተጨማሪ በጀት መመደቡን መግለጽ ይኖርበታል። እንደ ሌላው የት/ቤቶች ድጎማ በጀት ምደባ ይህ ድልድል መሠረት የሚያደርገው ድልድሉ ከመሠራቱ አንድ ዓመት ቀደም ብሎ በትምህርት አመራር መረጃ ስርዓት በተሰበሰበ መረጃ ነው፡፡ ይህ ሁኔታም ገንዘቡ በሚመደብበት ወቅት የሚኖረው የተማሪዎች ብዛት በፊተኛው ዓመት ከነበረው እንደሚጨምር ግምት ውስጥ ይገባል፡፡
- የስብሰባው ተሳታፊዎች ከ200 ተማሪዎች በታች ላሉዋቸው ት/ቤቶችና አ.መ.ት.ማ. በሚመደበው ገንዘብ ላይ ከተስማሙ ወደሚቀጥለው የስብሰባ አጀንዳ ያልፋሉ፡፡

የስብሰባ አጀንዳ ቁጥር 2፡- በወረዳው ልዩ ፍላጎት ላላቸው ተማሪዎች ከተመደበው 1% ተጨማሪ የት/ቤቶች ድጎማ በጀት ላይ በጀት የሚመደብላቸው ት/ቤቶችና አ.መ.ት.ማ. መለየትና መወሰን፡፡

- እያንዳንዱ ወረዳ ከክልል ወደ ወረዳው ልዩ ፍላጎት ላላቸው ተማሪዎች የተላከውን ገንዘብ ለት/ቤቶችና ለአ.መ.ት.ማ. የሚመደብበትን መንገድ ይወስናል፡፡
- እያንዳንዱ ወረዳ ለዚሁ አገልግሎት የተላከውን ገንዘብ በሙሉ ምንም ሳያስቀር ለሚመለከታቸው ት/ቤቶችና አ.መ.ት.ማ. መላክ ይኖርበታል፡፡
- ወረዳው ገንዘቡን ለሚመለከታቸው ልዩ ፍላጎት ያላቸው ተማሪዎች ላሉዋቸው ት/ቤቶችና አ.መ.ት.ማ. ሲልክ (በተማሪዎች ብዛት ወይስ ሁሉንም ችግሩ ያለባቸው ት/ቤቶች በሚያስፈልጋቸው የትምህርት መሣሪያ ማሟላትን በተመለከተ) ከክልል የሚላክለትን መመሪያ መጠቀም ይችላል፡፡.

- የስብሰባው ተሳታፊዎች ልዩ ፍላጎት ላላቸው ት/ቤቶች የተላከውን የት/ቤቶች ድጎማ በጀት በሚመደብላቸው ት/ቤቶችና አ.መ.ት.ማ. እንዲሁም መጠኑ ምን ያህል እንደሆነ ወስነው ከተስማሙ ወደሚቀጥለው አጀንዳ ያልፋሉ፡፡

አጀንዳ ቁጥር 3፡ ኦፊሲያላዊ የት/ቤቶች ድጎማ በጀት መመደቢያ ቅጽ አሞላል/መሙላት

- በዚህ ስብሰባ ላይ የሚታየው ሦስተኛው ጉዳይ ለትምህርት ቤቶችና አ.መ.ት ማዕከላት የሚሰጠውን ጠቅላላ የድጎማ በጀት መጠን ማስላት ነው፡፡
- የወ.ት.ጽ/ቤ እና የወ.ፋ.ኢ.ል.ጽ/ቤት ሠራተኞች ከዚህ መመሪያ አባሪ 3 ላይ ከት/ቤት ድጎማ በጀት አመዳደብ ከሚለው ቅጽ ላይ ከ'ሀ-በ' ያሉትን አምዶች መሙላት አለባቸው፡፡ እነዚህ አምዶች ከታች በሰንጠረዥ 6 ላይ ለምሳሌነት ቀርበዋል፡፡ እያንዳንዱ አምድ ከታች በቅደም ተከተል ተብራርቷል፡፡

    1. የት/ቤቶች ድጎማ በጀት አመዳደብ ቅጹን ለመሙላት በመጀመሪያ በወረዳው ውስጥ የሚገኙትን ት/ቤቶችና የአ.መ.ት ማዕከላት በአምድ ሀ' ስር ያሰፍራሉ፡፡ ከዚያም አምድ 'ለ'፣ 'ሐ'፣ 'መ'፣ 'ሠ'፣ 'ረ' እና 'ሰ' ን ይሞላሉ፡፡ በሁሉም ት/ቤቶችና አ.መ.ት ማዕከላት የተመዘገበው የተማሪዎች ቁጥር መረጃ በቅርብ ጊዜ በፌደራል የት.አ.መ.ሥ ከተሰበሰበ መረጃ የተወሰደ መሆን አለበት (የድጎማ በጀቱ ከሚመደብበት የትምህርት ዘመን በፊት የነበረው ዓመት መረጃ)፡፡
    2. የተመደበውን መደበኛ የት/ቤቶች ድጎማ በጀት አስልቶ በዓምድ 'ሸ' ማፈር፤ ስሌቱ በተማሪዎች ብዛትና ከዓምድ 'ሐ-ሰ' ባለው የእያንዳንዱ ደረጃ የተመደበውን ዝቅተኛ መጠን መሠረት ያደረገ ነው፡፡ ይህ ድምር ከክልል ት/ቢሮ ለወረዳው በተላከው ደብዳቤ ላይ ከሠፈረው ድምር/መጠን ጋር እኩል መሆን ይኖርበታል፡፡
    3. የስብሰባ አጀንዳ ቁጥር 1ን መሠረት በማድረግ ከ200 ተማሪዎች በታች ላሉዋቸው ት/ቤቶችና አ.መ.ት.ማ. የሚመደብ ካለ በዓምድ 'ቀ' ማስፈር፡፡
    4. ዓምድ 'በ' በስብሰባው አጀንዳ ቁጥር 2 መሠረት ልዩ የትምህርት ፍላጎት ያላቸው ተማሪዎች ላሉዋቸው ት/ቤቶችና አ.መ.ት.ማ. የሚመደበውን መጠን ማሳየት አለበት፡፡

5. ዓምድ ‘ተ’ ከ200 ተማሪዎች በላይ ላለው እያንዳንዱ የትምህርት ተቋም የተመደበ መደበኛ የትምህርት ቤቶች ድጎማ በጀት (በዓመድ ‘ሸ’ የተመለከተው) ወይም ያሉዋቸው ተማሪዎች ብዛት ከ200 በታች ከሆነ የተመደበውን ተጨማሪ የድጎማ በጀት (ማለትም ዓምድ ‘ቀ’) እና በዓምድ ‘በ’ የተመለከተው ለልዩ ፍላጎት ተማሪዎች የተመደበ ድምር (ማለትም ተ=‘ሸ’+‘ቀ’+‘በ’) ይሆናል:: ለትንንሽ ት/ቤቶችና አ.መ.ት.ማ. የተመደበው መጠን መደበኛውን የት/ቤቶች ድጎማ በጀት ይተካል (ሁለቱ አይደመሩም)፡፡
6. ቅፁ ከዓምድ ሀ-ከ ከተሞላ በኋላ ፎቶ ኮፒ (ኮፒ) ተደርጎ ዋናው በወረዳ ፋ.ኢ.ል ማት ጽ/ቤት ሲቀመጥ ኮፒው/ግልባጩ ደግሞ በወረዳ ት/ጽ/ቤት ይቀራል፡፡ ሁለቱም (ዋናውና ቅጅው/ኮፒው) ለምርመራ ሲፈለጉ በማንኛውም ጊዜ በሁለቱም ጽ/ቤቶች መገኘት አለባቸው፡፡

ተግባር 2 በተሳካ ሁኔታ መተግበሩን የሚያሳይ የውጤት መለኪያ	በወረዳ ፋ.ኢ.ል/ጽ.ቤት እና በወረዳ ትምህርት ጽ/ቤት የሚከተሉት ሰነዶች መገኘት፡ (1) የትምህርት ቤቶች ድጎማ በጀት ፋይል፣ (2) አጀንዳና ለወረዳው ትንንሽ ት/ቤቶችና አ.መ.ት.ማ. እንዲሁም ልዩ ፍላጎት ላላቸው ተማሪዎች የተመደበው ተጨማሪ የት/ቤቶች ድጎማ በጀት ዓይነትና መጠን ውሳኔን ጨምሮ የስብሰባዎች ቃለጉባኤ፣ (3) በአግባቡ/በትክክል የተሞላ የት/ቤቶች ድጎማ በጀት መመዝገቢያ ቅፅ (ዋናው በፋ.ኢ.ል. ጽ/ቤት፤ ኮፒው ደግሞ በወረዳ ት/ጽ/ቤት

ሰንጠረዥ 6ሀ፡- በወ.ት.ጽ/ቤት እና በወ.ፋ.ኢ.ጽ/ቤ የሚሞላ ኦፊሲያላዊ የት/ቤቶች ድጎማ በጀት መመደቢያ/መመዝገቢያ ቅፅ (ምሣሌ)

ዓ ም ድ	ሀ	ለ	ሐ	መ	ሠ	ረ	ሰ	ሸ	ቀ	በ	ተ

ቁ..	የተቋሙ ስም	የተቋሙ ዓይነት (1ኛ ደ.ት/ቤት፣ 2ኛ ደረጃ ት/ቤት፣ አ.መ.ት.ማ)	ከት.አ.መ.ስ. የተገኘ የተማሪዎች ብዛት መረጃና የብር መጠን በደረጃ					ጠቅላላ 'መደበኛ' የት.ድ.በ. (ብር)	ከ200 ተማሪዎች በታች ስላሉት ተጨማሪ የት.ቤ.ድ.በ. አለው? (አዎ/አይደለም) (ብር)	ለልዩ ፍላጎት ተጨማሪ የት.ድ.በ. አለው? (አዎ/አይደለም) (ብር)	ጠቅላላ የተመደበው የት.ቤ.ድ.በ. ድምር (ብር)
			ከ1-4	ከ4-8	አ.መ.ት.ማ.	ከ9-10	ከ11-12				
			(50 ብር)	*(55 ብር)*	*(50 ብር)*	*(60 ብር)*	*(70 ብር)*				
								ሸ = (ሐ*50) + (መ*55) + (ሠ*50) + (ረ*60) + (ሰ*70)	ከአጀንዳ ቁ.1	ከአጀንዳ ቁ.2	ተ+በ = ሸ+በ (ከ200 ተማሪዎች በላይ ላሉዋቸው ተቋማት ተ+በ = ቀ+በ (ትንሽ ተቋም ከሆነ)
1	ተቋም 1	1ኛ ደረጃ	654	245	-	-	-	46,175	አይደለም	**አዎ** 500	46,675
2	ተቋም 2	1ኛ ደረጃ	112	-	-	-	-	~~5,600~~	**አዎ** 10,000	አይደለም	10,000
3	ተቋም 3	አ.መ.ት.ማ.	-	-	380	-	-	19,000	አይደለም	**አዎ** 2,000	21,000
4	ተቋም 4	2ኛ ደረጃ	-	-	-	339	110	28,040	አይደለም	አይደለም	28,040

- **ተቋም 1**: ከ1-8 ክፍል ተማሪዎች ያሉት የመጀመሪያ ደረጃ ት/ቤት በነፍስወከፍ ተማሪ እንደ ክፍል ደረጃው ብር 50 እና ብር 55 ይመደብለታል፡፡ ስለዚህ ከት/ሚ የት.አ.መ.ስ. (EMIS) የተገኘውን የተማሪዎች ብዛት በዓምድ 'ሐ' እና በዓምድ 'መ' ይመዘገባል፡፡ የተቋሙ ተማሪዎች ቁጥር ከ200 በላይ ስለሆነ ለትንንሽ ተቋሞች የሚመደበው ተጨማሪ የድጎማ ገንዘብ በዓምድ 'ቀ' አይመዘገብለትም ማለት ነው፡፡ ልዩ ፍላጎት ላላቸው ተማሪዎች የሚታሰብ ግን ብር 500 ያገኛል፡፡ ስለዚህ ተቋም 1 የሚያገኘው ጠቅላላ ገንዘብ ብር **46,675** ይሆናል፡፡
- **ተቋም 2**: ከ1-4 ክፍል ተማሪዎች ያሉት የመጀመሪያ ደረጃ ት/ቤት በነፍስ ወከፍ ተማሪ ብር 50 ይመደብለታል፡፡ ስለዚህ ከት/ሚ የት.አ.መ.ስ. (EMIS) የተገኘውን የተማሪዎች ብዛት በዓምድ 'ሐ' ይመዘገባል፡፡ የተቋሙ ተማሪዎች ቁጥር ከ200 በታች ከለሆነ ለትንንሽ ተቋሞች የሚመደበው ተጨማሪ የድጎማ ገንዘብ በዓምድ 'ቀ' ይመዘገብለታል፡፡ ስለዚህ ተቋም 2 የሚያገኘው ጠቅላላ ገንዘብ ብር **10,000** ይሆናል፡፡
- **ተቋም 3**: አ.መ.ት.ማ. (ABE) በነፍስ ወከፍ ተማሪ ብር 50 ይመደብለታል፡፡ ስለዚህ ከት/ሚ የት.አ.መ.ስ. (EMIS) የተገኘውን የተማሪዎች ብዛት በዓምድ 'ሠ' ይመዘገባል፡፡ የተቋሙ ተማሪዎች ቁጥር ከ200 በላይ ስለሆነ ለትንንሽ ተቋሞች የሚመደበው ተጨማሪ የድጎማ ገንዘብ በዓምድ 'ቀ' አይመዘገብለትም ማለት ነው፡፡ ልዩ ፍላጎት ላለባቸው ተማሪዎች የሚታሰብ ግን ብር 2,000 ያገኛል፡፡ ስለዚህ ተቋም 3 የሚያገኘው ጠቅላላ ገንዘብ ብር **21,000** ይሆናል፡፡
- **ተቋም 4**: ከ9-12 ክፍል ተማሪዎች ያሉት ሁለተኛ ደረጃ ት/ቤት በነፍስ ወከፍ ተማሪ እንደ ክፍል ደረጃው ብር 60 እና ብር 70 ይመደብለታል፡፡ ስለዚህ ከት/ሚ የት.አ.መ.ስ. (EMIS) የተገኘውን የተማሪዎች ብዛት በዓምድ 'ረ' እና በዓምድ 'ሰ' ይመዘገባል፡፡ የተቋሙ ተማሪዎች ቁጥር ከ200 በላይ ስለሆነ ለትንንሽ ተቋሞች የሚመደበው ተጨማሪ የድጎማ ገንዘብ በዓምድ 'ቀ' አይመዘገብለትም ማለት ነው፡፡ ልዩ ፍላጎት ላላቸው ተማሪዎች (በዓምድ'በ') የሚታሰብም አይኖረውም፡፡ ስለዚህ ተቋም 4 የሚያገኘው ጠቅላላ ገንዘብ ብር **28,040** ይሆናል፡፡

ተግባር 3፡ ልዩ ፍላጎት ላላቸው ተማሪዎች የተመደበ ተጨማሪ በጀት ጭምር (ካለ) ለት/ቤቶችና አ.መ.ት. ማዕከላት የተመደበላቸውን የት/ቤቶች ድጎማ በጀት መጠን ማሳወቅ

- እያንዳንዱ ወረዳ የት/ቤት ድጎማ በጀት መመደቢያ ቅጹን ሞልቶ ከጨረሰ በኋላ ለሁሉም ት/ቤቶችና አ.መ.ት. ማዕከላት ለልዩ ፍላጎት ተማሪዎች የተመደበውን ጭምር በአጠቃላይ የሚደርሳቸውን የትምህርት ቤት ድጎማ በጀት እንዲሁም ለስሌቱ የተጠቀመበትን የተማሪዎች ምዝገባ መረጃና በነፍስ ወከፍ ለተማሪ የተመደበውን መጠን የሚገልጽ ደብዳቤ መላክ አለበት፡፡ ለምደባውም ከዚህ በታች ያለውን ሰንጠረዥ (ሰንጠረዥ 6ለ.) ተሞልቶ መላክ ይኖርበታል፡፡

ሰንጠረዥ 6ሀ፡- በወ.ት.ጽ/ቤት እና በወ.ፋ.ኢ.ጽ/ቤ የሚሞላ ኦፊሲያላዊ የት/ቤቶች ድጎማ በጀት መመደቢያ/መመዝገቢያ ቅፅ (ምሣሌ)

የተቋሙ ስም	የተቋሙ ዓይነት (1ኛ ደ.ት/ቤት፣ 2ኛ ደረጃ ት/ቤት፣ አ.መ.ት.ማ)	ከት.አ.መ.ስ. የተገኘ የተማሪዎች ብዛት መረጃና የብር መጠን በደረጃ					ጠቅላላ 'መደበኛ' የት.ድ.በ. (ብር)	ከ200 ተማሪዎች በታች ስላሉት ተጨማሪ የት.ቤ.ድ.በ. አለው? (አዎ/አይደለም) (ብር)	ለልዩ ፍላጎት ተጨማሪ የት.ድ.በ. አለው? (አዎ/አይደለም) (ብር)	ጠቅላላ የተመደበው የት.ቤ.ድ.በ. ድምር (ብር)
		ከ1-4	ከ4-8	አ.መ.ት.ማ.	ከ9-10	ከ11-12				
		(50 ብር)	*(55 ብር)*	*(50 ብር)*	*(60 ብር)*	*(70 ብር)*				
	ማስታወሻ: – የተማሪዎች ብዛትና መደበኛ የትምህርት ቤቶች ድጎማ በጀት ስሌት የተሠራው ከትምህርት ሚኒስቴር የትምህርት አመራር መረጃ ሥርዓት በተገኘው መረጃ መሠረት ነው፡፡ ይህ መረጃ የሚደርሰው ዘግይቶ ስለሆነ የ2008 ዓ.ም. ስሌት የተሰራው የ2006 ዓ.ም. መረጃና በየዓመቱ ሊጨምር የሚችለው የተማሪዎች ብዛት ከግምት ውስጥ በማስገባት ነው፡፡ – የተቋማቱ ተማሪዎች ብዛት ከ200 በታች ከሆነ ለትንንሽ ት/ቤቶች የተፈቀደውን ተጨማሪ የት/ቤቶች ድጎማ በጀት ይመደብለታል፡፡ ይህ በሚሆንበት ወቅት መደበኛው የድጎማ በጀት መጠን ለመጀመሪያ ደረጃ ት/ቤቶችና ለአ.መ.ት.ማ. በብር 10,000 እና ለ2ኛ ደረጃ ት/ቤቶች በብር 12,000 ይተካል፡፡ የተመደበው መደበኛ የድጎማ በጀት ከተጨማሪው የድጎማ በጀት የሚበልጥ ከሆነ የሚበልጠው (መደበኛው) መጠን ይወሰዳል፡፡									

ተግባር 3 በተሳካ ሁኔታ መተግበሩን የሚያሳይ የውጤት መለኪያ	(1) በወ.ት.ጽ.ቤ. እና ወ.ፋ.ኢ.ል.ጽ.ቤ. የሚገኙ ለትምህርት ቤቶችና አ.መ.ት ማእከላት የተላኩትን ደብዳቤዎች ግልባጭ የያዘ መዝገብ መኖር፡፡

ተግባር 4፡ ለትምህርት ቤቶችና የአ.መ.ት ማዕከላት የት/ቤት ድጎማ በጀት መስጠት

- የት/ቤቶች ድጎማ በጀት በወረዳው የባንክ አካውንት/ሂሳብ እንደደረሰ የወረዳው ት/ጽ/ቤትና የወረዳው ፋ.ኢ.ል.ጽ/ቤት የተመደበውን የት/ቤቶች ድጎማ በጀት ለእያንዳንዱ ት/ቤትና አ.መ.ት.ማ. በወቅቱ እንዲተላለፍ ማድረግ ይኖርባቸዋል፡፡
- ለየት/ቤቱና አ.መ.ት.ማ. የተመደበውን ገንዘብ የሚረከብ ሰው በተመለከተ መመሪያው በዚህ መመሪያ ክፍል 6 ላይ ይገኛል፡፡
- የወረዳው ፋ.ኢ.ል.ጽ/ቤት የት/ቤቶች ድጎማ በጀት መመደቢያ ቅጽ በትክክል በመሙላትና በመፈረም ለሚመለከታቸው ገንዘቡን የሚረከቡ ት/ቤቶችና አ.መ.ት.ማ. ተወካዮች መስጠት ይኖርበታል፡፡

ተግባር 4 በተሳካ ሁኔታ መተግበሩን የሚያሳይ የውጤት መለኪያ	(1) በትክክል የተሞላና የሚመለከታቸው ተቋማት ተወካዮች ስለመረከባቸው ፊርማ ያረፈበት ኦፊሲያላዊ የት/ቤቶች ድጎማ በጀት ምደባ ቅፅ መኖር፡፡

ተግባር 5፡ የት/ቤቶች ድጎማ በጀት ፕሮግራም አጠቃላይ ክትትል ማደረግ እንዲሁም ለት/ቤቶች እና አ.መ.ት. ማዕከላት ድጋፍ መስጠት

- የወ.ት.ጽ/ቤ. ሠራተኞችና የወረዳው የውስጥ ኦዲተሮች የት/ቤት ድጎማ በጀት ፕሮግራም አፈጻጸምን ለመቆጣጠር/ለማጣራት በት/ቤቶችና አ.መ.ት ማዕከላት የቁጥጥር ጉብኝት ማድረግ አለባቸው፡፡ ጉብኝቱ አዲስ የተጀመረውን የት/ቤቶች አንስፔክሽን ስርዓት ባለሙያዎችን ማካተት ይኖርበታል፡፡
- የሚደረጉት የክትትልና ድጋፍ ጉብኝቶች በሚከተሉት ሦስት ጊዚያት ቢካሄዱ ይመረጣል፡-

1. **በየትምህርት ዘመኑ መጨረሻ፡-** የወረዳ ሠራተኞች ት/ቤቶችና አ.መ.ት.መ. ቀጣይ የትምህርት ዘመን የት/ቤት መሻሻል ዕቅዳቸውን በሚገባ እንዲያዘጋጁ ጉብኝት በማድረግ ተገቢውን ድጋፍ ማድረግ ይኖረባቸዋል፡፡ በዚህ ወቅት የሚደረገው ድጋፍ ወ.ተ.መ.ህ. መረጃን መሠረት ያደረገ ዕቅድ እንዲያዘጋጅ ለማድረግ ተገቢውን ድጋፍ ይሰጣል፡፡ ት/ቤቶችና አ.መ.ት.ማ. ከሚላክላቸው የድጎማ በጀት ቢያንስ 50% ለመማር ማስተማር ርዕሰ ጉዳይ /domain/ ማዋል እንደሚገባቸው ማስታወስ ያስፈልጋል፡፡

2. **የት/ቤቶች ድጎማ በጀት ለተቋማቱ እንደተለቀቀ/እንደተላከ፡-** የወረዳ ሠራኞች ተቋማቱ(ት/ቤቶችና አ.መ.ት.ማ.) የተመደበላቸውን በጀት በአግባቡ በመጠቀም ፕሮግራሙን በውጤት ለመተግበር እንዲችሉ ተገቢውን ምክርና ድጋፍ ለመስጠት እንደ አስፈላጊነቱ ጉብኝት ማድረግ ይኖርባቸዋል፡፡
3. **የት/ቤቶች ድጎማ በጀቱ ከተላከ ከሦስት ወራት ገደማ በኋላ፡-** የወረዳ ሠራተኞች በዚህ ወቅት ት/ቤቶችና አ.መ.ት.ማ. ተገቢውን ሰነድ አደራጅተው ማስቀመጣቸውን ለማረጋገጥ ጉብኝት ማድረግ ይኖርባቸዋል፡፡ ሰነዶቹ፡- የት/ቤቶች ድጎማ በጀት መመዝገቢያ ደብተር/Grants Cash Book እና ተዛማጅ ሰነዶች (አባሪ 5 ይመልከቱ)፣ የት/ቤቶች መሻሻል/ድጎማ በጀት ፕሮግራም የቅድሚያ ትኩረቶች ቅፅ (አባሪ 4 ይመልከቱ)፣ እና የት/ቤቶች ድጎማ በጀት ፋይል ያካትታሉ፡፡ የወረዳ ትምህርት ጽ/ቤት ሠራተኞች የድጎማ በጀቱ በት/ቤት መሻሻል ዕቅድ ተለይተው ለተቀመጡ ተግባራት በትክክል ሥራ ላይ መዋሉን ማረጋገጥ ይኖርባቸዋል፡፡ የባሰ የአቅም ውስንነት ሊኖርባቸው ስለሚችል ቅድሚያ የመስክ ጉዞ ጉብኝቱ ወደ አ.መ.ት.ማ. መሆን አለበት፡፡

ተግባር 5 በተሳካ ሁኔታ መተግበሩን የሚያሳይ የውጤት መለኪያ	(1) በእያንዳንዱ ጉብኝት ወቅት የተጠናቀረ ሪፖርት በወረዳዎች መገኘት፡፡

ክፍል 6 ፡ በት/ቤትና በህብረተሰቡ ደረጃ የሚሰራባቸው መመሪያዎች

6.1. የወ.ተ.መ.ህ ኃላፊነቶች

የወ.መ.ህ ለት/ቤት ድጎማ በጀት የተመደበውን ገንዘብ በትምህርት ቤቶችና አ.መ.ት ማዕከላት ውስጥ የመቆጣጠር ኃላፊነት ይኖረዋል፡፡ ት/ቤቶች በጀቱን በሥራ ላይ በማዋል ረገድ ሙሉ ኃላፊነት ይኖራቸዋል፡፡ በት/ቤቱ ወይም በአ.መ.ት.ማ. ውስጥ እስከአሁን የወ.ተ.መ.ህ ካልተቋቋመ መቋቋም ይኖርበታል፡፡ የወ.ተ.መ.ህ የሚከተሉት ኃላፊነቶች ይኖሩታል፡፡

ተግባር 1፡ በት/ቤቶች ድጎማ ፕሮግራም አተገባበር ለወ.ተ.መ.ህ. ግንዛቤ ማስጨበጥና ለማህበረሰብ የግንዛቤ ማስፋፊያ መድረክ ማዘጋጀት

ተግባር 2፡ የት/ቤቶች ድጎማ በጀቱን በሚመለከት የህብረተሰቡ ግንዛቤ ማስፋፊያ ስብሰባ ማካሄድ

ተግባር 3፡ ከት/ቤቶች የድጎማ በጀት ጋር የተያያዙ ሰነዶች በየጊዜው ማሻሻልና አደራጅቶ ማስቀመጥ

ተግባር 4፡ በት/ቤት መሻሻል ዕቅድ ውስጥ ልዩ ድጋፍ የሚያስፈልጋቸው ተማሪዎች ጉዳይ ማካተት (ለዚህ ጉዳይ የተመደበ በጀት ካለ)

ተግባር 5፡ የትምህርት ቤቶች ድጎማ በጀት ገንዘብን መቀበል

ተግባር 6፡ የትምህርት ቤት መሻሻል ዕቅድ መተግበር

ተግባር 7፡ የፋይናንስ አጠቃቀም ሁኔታን የሚገልፅ መረጃ በት/ቤቶች ድጎማ በጀት የማስታወቂያ ሰሌዳ መለጠፍ፡፡

ተግባር 1፡ በት/ቤቶች ድጎማ ፕሮግራም አተገባበር ለወ.ተ.መ.ህ. ግንዛቤ ማስጨበጥና ለማህበረሰብ የግንዛቤ ማስፋፊያ መድረክ ማዘጋጀት

- የወ.ተ.መ.ህ ሊቀመንበሩ በወረዳ ደረጃ ለአንድ ቀን (ሁለት ምሽቶች) በሚካሄድ የት/ቤት ድጎማ በጀት አመዳደብ ስልጠናና ወርክሾፕ ላይ ተሳትፎ ከተመለሰ በኋላ ከትምህርት ቤቱ ርዕሰ መምህር ጋር በመተባበር በወ.ተ.መ.ህ. ውስጥ በኃላፊነት ከሚያገለግሉት ግለሰቦችና ሌሎች የት/ቤቱ ሰራተኞች ጋር ስለ ት/ቤቶች ድጎማ በጀት ፕሮግራም እና የት/ቤቶች ድጎማ በጀት ግንዛቤ ለማስጨበጥ ስብሰባ ያካሂዳል፡፡

- በተመሳሳይ መንገድ በስብሰባው የተሳተፉ የት/ቤቶች እና የወ.ተ.መ.ህ. ተወካዮች ለሌሎች የት/ቤቱ ማህበረሰብ አባላትና ለአ.መ.ት.ማ. አሳላጮች ግንዛቤውን ማስጨበጥ አለባቸው፡፡
- ከወ.ተ.መ.ህ. የግንዛቤ ማስጨበጫ ስብሰባው በማስከትል ወ.ተ.መህ. የአካባቢውን ማህብረሰብ ተመሳሳይ ግንዛቤ የሚያስጨብጥበትና የድጎማ በጀቱን አዋጪ አጠቃቀም አስተያየት የሚሰበስብበት መድረክ ያዘጋጃል፡፡ ይህንን ስብሰባ ሲያቅድ ለሚከተሉት ጉዳዮች ትኩረት መስጠት ያስፈልጋል፡፡

1. በማህበረሰቡ የግንዛቤ ማስጨበጫ ስብሰባ ወ.ተ.መ.ህ. ቃለጉባኤ የሚይዝ ሰው መመደብ ይኖርበታል፡፡ ቃለ ጉባኤውም በት/ቤቶች ድጎማ ፕሮግራም የስብሰባ መዝገብ መስፈርና መቀመጥ ይኖርባታል፡፡ (ለዝርዝሩ ተግባር 3ን ይመልከቱ)
2. ስለ ት/ቤቶች ድጎማ ፕሮግራም በቂ ግንዛቤ ማግኘት ስለሚኖርባቸው በተቻለ መጠን የማህበረሰቡን አባላት በስብሰባው ላይ እንዲገኙ ማድረግ እጅግ አስፈላጊ ነው፡፡
3. ከማህበረሰቡ የሚጋበዙት ተሳታፊዎች የአ.መ.ት.ማ. ሠራኞች፣ ወላጆች፣ እና የአ.መ.ት.ማ. የሚደግፉ የማህበረሰቡ አባላትን ያካትታል፡፡
4. ይህንን ሁለት ሰዓታት ሊወስድ የሚችል ስብሰባ ሁሉም ተሳታፊዎች መገኘት በሚችሉበት ቦታና ስዓት ማካሄዱ አስፈላጊ ነው፡፡
5. በህብረተሰቡ የግንዛቤ ማስጨበጫ ስብሰባ ወቅት ወ.ተ.መ.ህ. ስብሰባውን ማን በሊቀመንበርነት መምራት እንዳለበት በመወሰን በሚመረጠው ሰብሳቢ መስማማቱን ማረጋገጥ ያስፈልጋል፡፡ የሚመረጠው አካል ስብሰባውን የመምራት ሚናውን በተገቢው መንገድ መወጣት አለበት፡፡

ተግባር 1 በተሳካ ሁኔታ መተግበሩን የሚያሳይ የውጤት መለኪያ	(1) የተሳታፊዎችን ዝርዝር ያካተተ የወ.ተ.መ.ህ. ስብሰባ ቃለ ጉባኤ በት/ቤቶች ድጎማ በጀት ፕሮግራም የቃለ ጉባኤ መዝገብ ተደራጅቶ መገኘት፡፡ (2) የማህበረሰብ ግንዛቤ ማስጨበጫ ስብሰባ ዕቅድ

ተግባር 2፡ የት/ቤት ድጎማ በጀቱን በሚመለከት የወላጆችና የህብረተሰቡ ግንዛቤ ማስፊያ ስብሰባ ማዘጋጀት

- የስብሰባው አዘጋጆች (ማለትም የወ.መ.ህ ሊቀመንበር እና ወይም የወ.መ.ህ አባል እና ወይም የት/ቤቱ ርእሰ መምህር) የስብሰባውን ተሳታፊዎች እንኳን ደህና መጣችሁ በማለት ራሳቸውን በማስተዋወቅ ይጀምራሉ፡፡ ከዚህ በመቀጠል በሚከተሉት የስብሰባ ነጥቦች ላይ ይወያያሉ፡-

የስብሰባ አጀንዳ ቁጥር 1- የት/ቤት የድጎማ በጀት ፕሮግራሙን ማስተዋወቅ

- የስብሰባው አደራጆች በዚህ መመሪያ ክፍል አንድ ላይ የቀረቡትን ነጥቦች በመከለስ ስለ ት/ቤት ድጎማ በጀት ፕሮግራም ማብራሪያ ይሰጣሉ፡፡ እነዚህም፡-
    - የሁለተኛው ምዕራፍ አጠቃላይ ትምህርት ጥራት ማሻሻያ ፕሮጀክት የትኩረት አቅጣጫ ለውጥ፡
    - የትምህርት ቤቶች ድጎማ በጀት አመዳደብ ፕሮግራም ምንድነው?
    - የትምህርት ቤች ድጎማ በጀት ፕሮግራም ዋና ዋና ገጽታዎች ምንድን ናቸው?
    - የት/ቤች ድጎማ በጀቱ መጠን ምን ያህል ነው?
    - ለትምህርት ቤቶች የሚሰጠው የድጎማ በጀት ለምን ዓላማ ጥቅም ላይ ሊውል ይችላል?
    - የትምህርት ቤቶች የገንዘብ አጠቃቀም ግምገማ፤
    - በት/ቤቶች ድጎማ በጀት ፕሮግራም አስተዳርና በበጀቱ አጠቃቀም የተጠያቂነት ስርዓት መዘርጋቱ፤
    - በተለያየ ደረጃ በትምህርት ቤቶች ድጎማ በጀት ፕሮግራም አስተዳደር ላይ የሚገኙት ኃላፊዎች ሃላፊነቶች/ግዴታዎች ምንድን ናቸው? ተጠያቂነት እንዳለባቸው እንዲሁም ማህበረሰቡ ተጠያቂነት መኖሩን እንዲገነዘብና ክትትል እንዲያደርግ ምን መምሰል አለባቸው?
- የስብሰባው አዘጋጆች የትምህርት ቤቶች ድጎማ በጀት ባለፉት 4 ዓመታት ያመጣውን ለውጥ፣ ያጋጠሙ ችግሮችና ለችግሮቹ የተወሰደው መፍትሔ በዝርዝር መግለፅ ይኖርባቸዋል፡፡

- የስብሰባው አስተባባሪዎች በየዓመቱ የሚሰጠው የት/ቤቶች ድጎማ በጀት ወላጆችና ሕብረተሰቡ ለሚያደርጉት የገንዘብ ድጋፍ ለመደጎም መሆኑንና ሲደረግ የነበረውን ድጋፍ ለመተካት አለመሆኑን ግልጽ ማድረግ ይኖርባቸውል።፡፡
- በእነዚህ ነጥቦች ላይ ከተወያዩ በኋላ የስብሰባው አደራጅ በዓመቱ ለት/ቤቶች የሚሰጠው የድጎማ በጀት ምን ያህል ገንዘብ ለት/ቤቱ ወይም አ.መ.ት ማዕከሉ እንደተመደበለት መግለጽ አለበት፡፡
- ከዚያም የስብሰባው አደራጅ ተሳታፊዎች ጥያቄ ካላቸው እንዲያቀርቡ እድል ይሰጣል፡፡ ይህ የት/ቤቶች ድጎማ በጀት መመሪያ የሚነሱትን ጥያቄዎች ለመመለስ እንደ መረጃ መጠቀም ያገለግላል፡፡
- ሁሉም ተሳታፊዎች የት/ቤት የድጎማ በጀት ፕሮግራምን ምንነት በሚገባ ከተረዱ በኋላ የስብሰባው አዘጋጅ ወደቀጣዩ አጀንዳ መሸጋገር አለበት፡፡

የስብሰበ አጀንዳ ቁጥር 2፡- የት/ቤት ማሻሻያ እቅድ ማብራሪያ

- የስብሰባው አደራጆች ስለ ትምህርት ቤት ማሻሻያ እቅድ ምንነትና የትምህርት ጥራት ለማሻሻል (መጠነ ማቋረጥንና መድገምን ለመቀነስ፣ በሁሉም የትምህርት ዓይነቶች የፈተና ውጤትን ለማሻሻል፣ የመማራያና ማስተማሪያ ቁሳቁሶች አቅርቦትን ለማሻሻል፣ ወዘተ) የሚዘጋጅ እንደሆነ አጭር ማብራሪያ መስጠት አለባቸው፡፡
- የዚህ የስብሰባ ክፍል ዋነኛ ዓላማ በት/ቤት መሻሻል እቅዱ ላይ የሰፈሩትን ነጥቦች ለስብሰባው ተሳታፊዎች ለማስታወስ ነው፡፡
- የት/ቤት መሻሻያ ዕቅዱ ማብራሪያ አጭርና የስብበሳው ተሳታፊዎች በቀላሉ ሊረዱት የሚችሉ መሆን አለበት፡፡
- የስብሰባው አዘጋጆች ማብራሪያውን ከቀረቡ በኋላ ተሳታፊዎች ጥያቄ እንዲጠይቁ መጋበዝና በት/ቤት መሻሻያ እቅዱ ላይ ውይይት እንዲደረግ መጋበዝ አለባቸው፡፡
- ከውይይቱ በኋላ የስብሰባው አደራጆች ወደ ቀጣዩ አጀንዳ ማለፍ አለባቸው፡፡

የስብሰባ አጀንዳ ቁጥር 3- የትምህርት ቤቱ ድጎማ በጀት ጥቅም ላይ ሊውልባቸው የሚገቡ ቅድሚያ ትኩረት የተሰጣቸው ተግባራት ላይ የሚደረግ ውይይት

- የስብሰበው አዘጋጆች በት/ቤት መሻሻያ እቅዱ ላይ ማብራሪያ ካቀረቡ በኋላ በት/ቤት ማሻሻያ ዕቅዱ መሰረት ገንዘቡ ጥቅም ላይ ሊውልባቸው የሚገባቸውን ቅድሚያ ትኩረት የተሰጣቸው ተግባራት እንዲናገሩ ተሳታፊዎችን ይጠይቃሉ፡፡ የት/ቤት ድጎማ በጀት ገንዘብ በትምህርት ቤቱ ውስጥ የትምህርት ጥራትን ሊያሻሽሉ በሚችሉ ተግባራት ላይ መዋል እንዳለባቸው ግልጽ ማድረግ አስፈላጊ ነው፡፡
- ሁሉም ተሳታፊዎች ለት/ቤት ወይም ለአ.መ.ት.ማ. ከሚመደበው ገንዘብ ውስጥ ቢያንስ 50% መጠን ያለው ገንዘብ በት/ቤት መሻሻል ዕቅድ ለመማር ማስተማር ርዕሰጉዳይ/domain/ መዋል እንዳለበት እንዲያውቁ አበክሮ ማስገንዘብ/ማስታወስ ያስፈልጋል፡፡
- የት/ቤት ማሻሻያ ዕቅድ ለሌላቸው አ.መ.ት ማዕከላት የትምህርትን ጥራት ለማሻሻል በሚያስችሉ እንቅስቀቃሴዎች ላይ ውይይት መደረግና ዕቅድ እንዲያዘጋጁ የሚደረግበት መንገድ መኖር አለበት፡፡
- በስብሰባው ክፍል ውስጥ ጥቁር ሰሌዳ ካለ የስብሰባው አደራጆች ተሳታፊዎች ያቀረቧቸውን ተግባራት በዝርዝር በሰሌዳው ላይ በመፃፍ ሁሉም የቀረቡትን ሐሳቦች መመልከት እንዲችሉ ማድረግ አለባቸው፡፡
- ተሳታፊዎች የትምህርት ቤት ድጎማ በጀቱ ጥቅም ላይ በሚውልባቸው ቅድሚያ ትኩረት የተሰጣቸውን ተግባራት በሚገባ ተወያይተውበት ለመወሰን እንዲችሉ በቂ ጊዜ ሊኖራቸው ይገባል፡፡
- የት/ቤት ድጎማ በጀቱ ለምን ዓላማ ጥቅም ላይ መዋል እንዳለበት ከስምምነት ላይ እንደተደረሰ በዚህ መመሪያ አባሪ 4 ላይ በሰፈረው የት/ቤት ድጎማ በጀት ጥቅም ላይ የሚውልባቸው ቅድሚያ ትኩረት የተሰጣቸው ተግባራት መሙያ ቅጽ ላይ መስፈር አለበት፡፡ ይኸው መረጃ በትምህርት ቤቱ ድጎማ በጀት ማስታወቂያ ሰሌዳ ላይ መለጠፍ ይኖርበታል፡፡

የስብሰባ አጀንዳ ቁጥር 4 - በተሰብሳቢዎች መዝገብ ላይ መፈረም

- የመጨረሻው የስብሰባ አጀንዳ ተሳታፊዎች በተሰብሳቢዎች መዝገብ ላይ እንዲፈርሙ ማድረግ ነው፡፡ ሁሉም ተሳታፊዎች ስማቸውን መፃፍና በመዝገቡ ላይ መፈረም አለባቸው፡፡

- ይህ ተከናውኖ ሲጠናቀቅ የስብሰባው አስተባባሪዎች ሁሉም ተሳታፊዎች ላደረጉት አስተዋጽኦ በማመስገን ስብሰባውን ይደመድማሉ፡፡
- በስብሰባው መጨረሻ ላይ የስብሰባው አስተባባሪዎች የስብሰባውን ቃለ ጉባኤ በማዘጋጀት በት/ቤቶች ድጎማ በጀት ፕሮግራም የቃለጉባኤ መዝገብ ማስፈር አለባቸው፡፡

ተግባር 2 በተሳካ ሁኔታ መተግበሩን የሚያሳይ የውጤት መለኪያ	(1) በስብሰባው ላይ የተገኙት ተሳታፊዎች ስም ዝርዝር የያዘ የስብሰባው ቃለ ጉባኤ፡፡ (2) በትክክል የተሞላ የት/ቤቶች ድጎማ ፕሮግራም የቅድሚያ ትኩረት መመዘገቢያ ቅፅ በት/ቤቶች ድጎማ ፕሮግራም ፋይል መገኘትና ቅጅው በማስታወቂያ ሰሌዳ ተለጥፎ መገኘት፡፡

ተግባር 3፡ ከት/ቤቶች ድጎማ በጀት ጋር የተያያዙ ሰነዶችን በየጊዜው ማሻሻልና አደራጅቶ ማስቀመጥ

- የወ.ተ.መ.ህ በአራት ሰነዶች/ጉዳዮች ላይ ለመወያየት መሰብሰብ አለበት፡፡ ሰነዶቹን የመያዝና መረጃዎችን በየጊዜው የመመዝገብ ኃላፊነት ለማን እንደሚሰጥ ወ.ተ.መ.ህ. መወሰን አለበት፡፡ አንድ የወ.ተ.መ.ህ. አባል የሚከተሉትን ነጥቦች ጮክ ብሎ ማንበብ (ወይም ሌሎች አባላት እንዲያነቡለት መጠየቅ) ይኖርበታል፡፡

የት/ቤት የድጎማ በጀት ስብሰባ ቃለ ጉባኤ መዝገብ

- ወ.ተ.መ.ህ የት/ቤት ድጎማ በጀቱ ጥቅም ላይ የሚውልባቸው ተግባራትን ለመወሰን በሚደረጉ ስብሰባዎች የተያዙ ቃለ ጉባኤዎች የሚቀመጡበት መዝገብ የማዘጋጀት ኃላፊነት አለበት፡፡
- የአሠራር ሂደቶቹ በአግባብ ተግባራዊ መደረጋቸውን ለማረጋገጥ ወ.ተ.መ.ህ የሚያስተላልፉዋቸው ውሳኔዎች በሙሉ በቃለ ጉባኤው መዝገብ ላይ መስፈር አለባቸው፡፡
- የእያንዳንዱ ስብሰባ ቃለ ጉባኤ ስብሰባው የተደረገበትን ቀንና ቢያንስ የወ.ተ.መ.ህ ሶስት አባላትን ፊርማ መያዝ ይገባዋል፡፡
- የቃለ ጉባኤ መዝገቡን በአደራ የሚይዝ አንድ የወ.ተ.መ.ህ አባል መመረጥ አለበት፡፡

የት/ቤት ድጎማ በጀት መዝገብ/ፋይል

- ወ.ተ.መ.ህ የት/ቤት ድጎማ በጀት መዝገብ ማዘጋጀትና በየጊዜው ተገቢውን መረጃ በመዝገቡ ላይ ማስፈር አለበት፡፡ መዝገቡ የት/ቤት ድጎማ በጀቱን በሚመለከት የሚደረጉ ማናቸውንም የደብዳቤ ልውውጦች እንዲሁም ደረሰኞችንና የዋጋ ማቅረቢያዎችን የመሳሰሉ ማናቸውንም ጠቃሚ ሰነዶች ይይዛል፡፡
- በት/ቤት ድጎማ በጀት መዝገብ/ፋይል ውስጥ የሚያዘው መረጃ በሚገባ የተጠናቀረና ስርዝ ድልዝ የሌለው ሊሆን ይገባል፡፡
- የት/ቤት ድጎማ በጀት መዝገቡን የሚይዝ አንድ የወ.ተ.መ.ህ አባል መመረጥ አለበት፡፡

የት/ቤት የድጎማ በጀት የማስታወቂያ ሰሌዳ

- ወ.ተ.መ.ህ የት/ቤት ድጎማ በጀት እንዴት ጥቅም ላይ እንደሚውል የሚያሳይ መረጃ የሚለጠፍበት የት/ቤት ድጎማ በጀት የማስታወቂያ ሰሌዳ በግልጽ በሚታይ ቦታ መዘጋጀቱን ማረጋገጥ አለበት፡፡ በማስታወቂያ ሰሌዳው ላይ የሚለጠፈው መረጃ አቀራረብ በዚህ መመሪያ አባሪ 6 ላይ ይገኛል፡፡
- የት.ቤት ድጎማ በጀት ማስታወቂያ ሰሌዳው ህብረተሰቡ በቀላሉ ሊያየው በሚችለው ቦታ ላይ መቀመጥ ያለበት ሲሆን በዝናብና በፀሐይ እንዳይበላሽ ጥንቃቄ ሊደረግለት ይገባል፡፡
- የት/ቤት ድጎማ በጀት ማስታወቂያ ሰሌዳው ላይ የሚለጠፈው መረጃ ወቅታዊ መሆን አለበት፡፡

የሁለተኛው ምዕራፍ አጠቃላይ ትምህርት ጥራት ማሻሻያ ፕሮግራም የትምህርት ቤቶች ድጎማ በጀት የሒሳብ መዝገብ

- ወ.ተ.መ.ህ በትምህርት ቤቱ የድጎማ በጀት የሚያወጣቸውን ማናቸውንም ወጪዎች የሚመዘግብበት የሁለተኛው ምዕራፍ አ.ት.ጥ.ማ.ፕ የድጎማ በጀት የሂሳብ መዝገብ ማዘጋጀት አለበት፡፡ የሂሳብ መዝገቡ ትክክለኛና ስርዝ ድልዝ የሌለባቸው መረጃዎችን የሚይዝ መሆን አለበት፡፡ ይህ የሂሳብ መዝገብ የሚያገለግለው ትምህርት ቤቱ በአ.ት.ጥ.ማ.ፕ ስር ከወረዳ የተቀበለውን የት/ቤት ድጎማ በጀት ለመመዝገብ ብቻ መሆኑን ማስታወስ ያስፈልጋል፡፡ ት/ቤቱ ወይም አ.መ.ት ማዕከሉ

ከትምህርት ቤት ድጎማ በጀቱ ጋር ግንኙነት የሌላቸው ሌሎች የገቢ ምንጮች ወይም ወጪዎች ካሉት እነዚህ በሒሳብ መዝገቡ ላይ መስፈር አይኖርባቸውም፡፡ የሂሳብ መዝገቡ ምን እንደሚመስል በዚህ መመሪያ አባሪ 5 ላይ ተመልክቷል፡፡

ተግባር 3 በተሳካ ሁኔታ መተግበሩን የሚያሳይ የውጤት መለኪያ	ቀጥለው የተዘረዘሩትን ሰነዶች ወቅታዊ መሆን አለባቸው፡ (1) የት/ቤት ድጎማ በጀት ስብሰባ ቃለ ጉባኤ መዝገብ (2) የት/ቤት ድጎማ በጀት መዝገብ (3) የት/ቤት ድጎማ በጀት የማስታወቂያ ሰሌዳ እና (4) የትምህርት ቤት አ.ት.ጥ.ማ.ፕ የድጎማ በጀት የሂሳብ መዝገብ፡፡

ተግባር 4፡ በት/ቤት መሻሻል ዕቅድ ውስጥ ልዩ ድጋፍ የሚያስፈልጋቸው ተማሪዎች ጉዳይ ማካተት (የልዩ ፍላጎት ተማሪዎች ካሉና ለዚህ የተመደበ በጀት ካለ)

- የት/ቤት መሻሻል ዕቅድ በት/ቤቶች ድጎማ በጀት አማካኝነት ልዩ የትምህርት ፍላጎት ላላቸው ተማሪዎች በመማርና ማስተማር መስተጋብሩ ተሳትፎ እንዲኖራቸው ድጋፍ የሚሰጥበት መንገድ ማካተት ይኖርበታል፡፡ ይኸውም ለእነዚህ ተማሪዎች (ማለትም የማየት፣ የመስማት፣ የመማር፣ ወዘተ... ችግሮች ላሉባቸው) ተማሪዎች የሚያስፈልጉ አጋዥ ቁሳቁሶች/መሣሪያዎች ማቅረብን ማካተት ይኖርበታል፡፡
- ልዩ ፍላጎት ላላቸው ተማሪዎች የተመደበው ተጨማሪ የት/ቤቶች ድጎማ በጀት አካታች የሆነ የመማርና ማስተማር አካባቢ ለማበረታታትና ችግሩ ያለባቸውን ተማሪዎች መማር እንዲችሉ ለማድረግ ነው፡፡
- በልዩ የትምህርት ፍላጎት ጉዳዮች ዙሪያ ውስንነት ያለባቸው ት/ቤቶችና ወረዳዎች በተገኘው አጋጣሚ ከሚከተሉት ድጋፍ እንዲያገኙ መደረግ ይኖርበታል፡፡
    1. ከወረዳ፣ ከዞን ወይም ከክልል የልዩ ትምህርት ፍላጎት ባለሙያዎች፤
    2. የመምህራን ትምህርት ኮሌጆች፤
    3. በተለይ በልዩ ፍላጎት ትምህርት የሚሠሩ ት/ቤቶች፤
    4. አግባብ ያላቸው መምህራንና የልዩ ፍላጎት ትምህርት ማዕከል፤
    5. የአካል ጉዳተኞች ማህበራት እና መንግስታዊ ያልሆኑ ድርጅቶች ሊሆኑ ይችላሉ።
- በቀላል ዋጋ ሊገኙ የሚችሉ ልዩ የትምህርት ፍላጎት ያላቸውን ተማሪዎች ለመርዳት የሚያገለግሉ ቁሳቁሶች ምሳሌዎች ከዚህ በታች ተዘርዝረዋል፡፡

1. መስማትና ማየት የተሳናቸው ህፃናትን ለመለየት የሚያስችሉ፣ ለማየት የሚያገለግሉ መነፅሮችና ለመስማት የሚያግዙ መሣሪያዎች (ምሳሌ Snellen chart)፤
2. የልዩ ፍላጎት ትምህርትን በተመለከተ አጫጭር የግንዛቤ ማስጨበጫ ስልጠናዎች ማካሄድ፡፡ ይኸውም እንደ ብሬይል፣ የምልክት ቋንቋ፣ ወዘተ... የመሳሰሉትን ቁሳቁሶች በመጠቀም ማካሄድ ይቻላል፣
3. ልዩ ፍላት ያላቸው ህፃናት ያሉዋቸውን ቤተሰቦች መጎብኘትና ልጆቻቸውን ወደ ት/ቤት እንዲልኩ ማበረታታት፣
4. የቀለም ጽሑፎችን ወደ ብሬይል መቀየር፣
5. እንደ Jaws እና ሌሎች ሶፍትዌሮች በኮምፒዩተሮች በመጫን፣
6. ልዩ ድጋፍ የሚያስፈልጋቸውን ህፃናት በተለይ በአካታች ት/ቤቶችና በአፀደ ህፃናት የሚገኙትን ልዩ ድጋፍ መስጠት፣
7. ማየት ለተሳናቸው ህፃናት እንደ አባከስ የመሳሰሉ የትምህርት መርጃ መሣሪያዎችን ማቅረብ፡፡
8. የማየት ችግር ላለባቸው ህፃናት መፃፊያ ጣውላዎችና ስታይለስ ማቅረብ፣
9. የምልክት ቋንቋ መዝገበ ቃላቶችን ማቅረብ፣.

ተግባር 4 በተሳካ ሁኔታ መተግበሩን የሚያሳይ የውጤት መለኪያ	(1) በየዓመቱ ትምህርት የሚጀምሩ ልዩ ፍላት ያላቸው ተማሪዎች ቁጥር መጨመር፡፡

ተግባር 5፡ የትምህርት ቤቶች ድጎማ በጀት ገንዘብን መቀበል

- ለመጀመሪያና ሁለተኛ ደረጃ ት/ቤቶች ለትምህርት ቤቱ የተመደበውን የድጎማ በጀት የመቀበልና የመፈረም ኃላፊነቱ የት/ቤቱ ርዕሰ መምህር ይሆናል፡፡
- ለአ.መ.ት. ማዕከላት ደግሞ ከማዕከሉ ጋር ግንኙነት ያለው የክላስተር ት/ቤት ርዕሰ መምህር/ ወይም የአ.መ.ት. ማዕከሉ ወ.ተ.መ.ህ. ሊቀመንበር ገንዘቡን መቀበልና መፈረም ይችላሉ፡፡ የአ.መ.ት. ማዕከሉ ከክላስተር ሪሶርስ ማዕከል ጋር የተገናኘ ካልሆነ ወ.ተ.መ.ህ ከሌላው ንቁ ተሳትፎ የሚያደርግ የሕብረተቡ አባል የአ.መ.ት. ማዕከሉ ድጋፍ ሰጪ ገንዘቡን እንዲቀበል ሊመርጥ የሚችል ሲሆን የወ.ተ.መ.ህ ከሌለ በተቻለ ፍጥነት መቋቋም ይኖርበታል፡፡
- የትምህርት ቤቱ ርዕሰ መምህር ወይም የአ.መ.ት. ማዕከሉ ተወካይ የበጀት ገንዘቡን ሲቀበል የት/ቤት የድጎማ በጀት አመዳደብ ቅጽ ላይ መፈረም ይጠበቅበታል፡፡

- በሁለተኛው ምዕራፍ የአጠቃላይ ትምህርት ጥራት ማሻሻያ ፕሮግራም ወቅት የት/ቤቶች ድጎማ በጀት በሚመለከታቸው ት/ቤቶችና አ.መ.ት.ማ. በወቅቱ መድረሱን ለማረጋገጥና ለመከታተል ለርዕሰ መምህራን ወይም ወ.ተ.መ.ህ በመደወል መረጃ ማግኘት ይቻል ዘንድ የሞባይል ቴክኖሎጂ በሙከራ ደረጃ በሥራ ላይ ይውላል፡፡

ተግባር 5 በተሳካ ሁኔታ መተግበሩን የሚያሳይ የውጤት መለኪያ	(1) ት/ቤቶች እና አ.መ.ት.ማ. የት/ቤቶች ድጎማ በጀት መቀበላቸውን በማረጋገጥ የፈረሙበት ደረሰኝ/ሰነድ በ ወ.ፋ.አ.ል.ጽ.ቤ. መገኘት፡፡

ተግባር 6፡ የትምህርት ቤት ማሻሻያ እቅዱን በሥራ ላይ ማዋል/መተግበር

- የት/ቤት ድጎማ ገንዘቡ ገቢ እንደተደረገ ወዲያውኑ የወ.ተ.መ.ህ የት/ቤት ድጎማ በጀት ጥቅም ላይ የሚውልባቸውን የቅድሚያ ትኩረት የተሰጣቸው ተግባራት መሙያ ቅጽ (አባሪ 4) ላይ ለሰፈሩት ተግባራት ሊያውለው ይችላል፡፡
- የወ.ተ.መ.ህ ማናቸውንም ወጪዎች በአ.ት.ጥ.ማ.ፕ የት/ቤት ድጎማ በጀት ሂሳብ መዝገብ ላይ መመዝገብ አለበት፡፡
- የወ.ተ.መ.ህ የት/ቤት ድጎማ በጀቱ እንዴት እንደተሰራበት የሚያሳይ በጥሩ ሁኔታ የተያዘ መዝገብ ሊኖረው ይገባል፡፡

ተግባር 6 በተሳካ ሁኔታ መተግበሩን የሚያሳይ የውጤት መለኪያ	ቀጥለው የተዘረዘሩትን ሰነዶች ወቅታዊ መሆንና ተደራጅተው መገኘት አለባቸው፡ (1) የት/ቤት መሻሻል ዕቅድ (2) የት/ቤቶች ድጎማ በጀት የስብሰባ ቃለ ጉባኤ መዝገብ (3) የት/ቤት ድጎማ በጀት መዝገብ/ፋይል (4) የት/ቤት ድጎማ በጀት የማስታወቂያ ሰሌዳ እና (5) የሁለተኛው ምዕራፍ አ.ት.ጥ.ማ.ፕ. በጀት የሂሳብ መዝገብ

ተግባር 7፡ የፋይናንስ አጠቃቀም ሁኔታን የሚገልፅ መረጃ በት/ቤቶች ድጎማ በጀት የማስታወቂያ ሰሌዳ መለጠፍ

- በገንዘብ አያያዝ ረገድ ግልጽነትና ተጠያቂነት እንዲኖር ለማድረግ ት/ቤቶችና አ.መ.ት. ማዕከላት አጠቃላይ ወጪና ገቢዎችን እንዲሁም የት/ቤት ድጎማ በጀቱን የሚመለከቱ ዝርዝር ጉዳዮች የሚያካትት ዓመታዊ ሪፖርት መዘጋጀት አለበት፡፡
- ሪፖርቱ በየዓመቱ ሐምሌ 1 ላይ ተዘጋጅቶ መጠናቀቅ ይኖርበታል፡፡
- ዓመታዊ ሪፖርቱ ከተመደበው የድጎማ በጀት ቢያንስ 50% የሚሆነው ት/ቤት መሻሻል መርሀ ግብር ለመማር ማስተማር ርዕሰ ጉዳይ/domain/ መዋል አለመዋሉን በጉልህ ማሳየት ይኖርበታል፡፡
- የዚህን ሰነድ ናሙና አባሪ 6 ላይ መመልከት ይቻላል፡፡ ቅጹ ሙሉ በሙሉ ከተሞላ በኋላ በት/ቤት ድጎማ በጀት ማስታወቂያ ሰሌዳ ላይ መለጠፍ አለበት፡፡

ተግባር 7 በተሳካ ሁኔታ መተግበሩን የሚያሳይ የውጤት መለኪያ	(1) በትክክል የተሞላ የፋይናንስ ዝርዝር ሪፖርት (ቅፅ 6) በት/ቤቶች ድጎማ በጀት የማስታወቂያ ሰሌዳ መለጠፍ፡፡

አባሪዎች

አባሪ 1፡ በተለያዩ ደረጃዎች ላይ ያሉ ኃላፊነቶች የሚያሳይ ማጠቃለያ

ደረጃ	ኃላፊነት ያለው ድርጅት	ቅልፍ ግዴታ /Key Rseponsiblitis /
በፌደራል ደረጃ	• የትምህርት ሚኒስቴር ዕቅድ ዝግጅትና ህብት ማፈላለግ ዳይሬክቶሬት (ዕ.ዝ.ህ.ማ.ዳ.) • የትምህርት ሚኒስቴር የትምህርት ቤት መሻሻል ፕሮግራም ዳይሬክቶሬት (ት.መ.ፕ.ዳ.) • የገንዘብና ኢኮኖሚ ልማት ሚኒስቴር	• ተግባር 1፡ የትምህርት ቤት የድጎማ በጀት አመዳደብ መመሪያውን መተርጎም ማተምና ማሰራጨት • ተግባር 2፡ ለት/ቤት በጀት አመዳደብ መመሪያ የክልል አሰልጣኞች ወርክሾፕ ማደራጀት • ተግባር 3፡ ለት/ቤቶች የድጎማ በጀት የሚመደበውን ገንዘብ ለክልሎች የመላክ ሥራ ማቀናጀት • ተግባር 4፡ የትምህርት ቤቶች ድጎማ በጀት አጠቃቀም ጥናት ማካሄድ • ተግባር 5፡ ከጥናቱ በተገኘው መረጃ መሰረት በት/ቤቶች ድጎማ በጀት ፕሮግራም ላይ ውይይት የሚያካሂድበትን ወርክሾፕ ማደራጀት
በክልል ደረጃ	• የክልል የትምህርት ቢሮ (ክ.ት.ቢ.) • የክልል ፋይናንስና ኢኮኖሚ ልማት ቢሮ (ፋ.ኢ.ል.ቢ.)	• ተግባር 1. የት/ቤት ድጎማ በጀት አመዳደብ መመሪያውን በሚመለከት በዞን እና ወረዳ ደረጃ የሥልጠና ወርክሾፖችን ማደራጀት • ተግባር 2. አካታች ትምህርትን ለማበረታታትና ልዩ የትምህርት ፍላጎት ያላቸውን ህፃናት ጥራት ያለው የትምህርት ዕድል እንደያገኙ ለመርዳት ልዩ የትምህርት ፍላጎት ላላቸው ተማሪዎች ባሉባቸው ት/ቤቶች ተጨማሪ ድጎማ በጀት መመደብ • ተግባር 3. የት/ቤት ድጎማ በጀት አመዳደብን የሚያሳዩ ደብዳቤዎች ለወረዳዎች ማሰራጨት • ተግባር 4. የትምህርት ቤቶች ድጎማ በጀት ፕሮግራሙን መቆጣጠር
በዞን ደረጃ	• የዞን ትምህርት ጽ/ቤት (ዞ.ት.ጽ.ቤ.)	• ተግባር 1. የወረዳ የት/ቤት ድጎማ በጀት ስልጠና ወርክሾፖችን በበላይነት መቆጣጠር • ተግባር 2. የትምህርት ቤት የድጎማ በጀት ፕሮግራሙን መቆጣጠር
በወረዳ ደረጃ	• የወረዳ ትምህርት ጽ/ቤት (ወ.ት.ጽ.ቤ.) • የወረዳ ፋይናንስና ኢኮኖሚ ልማት ጽ/ቤት (ወ.ፋ.ኢ.ል.ጽ.ቤ.)	• ተግባር 1. የወረዳው የት/ቤት ድጎማ በጀት ስልጠና ወርክሾፖችን ማደራጀት • ተግባር 2. ለእያንዳንዱ ት/ቤትና የአ.መ.ት ማዕከል የድጎማ በጀት መመደብ • ተግባር 3. ለልዩ ፍላጎት ተማሪዎች የሚመደብ ተጨማሪ በጀትን (ካለ) ጨምሮ ስለ ት/ቤት የድጎማ በጀት አመዳደብ ለት/ቤቶችና አ.መ.ት ማዕከላት ማሳወቅ • ተግባር 4. ለትምህርት ቤቶችና የአ.መ.ት ማዕከላት የት/ቤት ድጎማ በጀት መስጠት • ተግባር 5. ለትምህርት ቤቶችና የአ.መ.ት ማዕከላት ድጋፍ መስጠት፣ የት/ቤት ድጎማ በጀት ፕሮግራሙን መቆጣጠር
በት/ቤትና በህብረተሰብ ደረጃ	• የት/ቤት አስተዳደር ኮሚቴ (ት.አ.ኮ) • የወላጅ፣ ተማሪዎች፣መምህራን ህብረት (ወ.ተ.መ.ህ)፣አ.መ.ት. ማዕከል አሳላጮች	• ተግባር 1. የወላጆችንና የሕብረተሰቡን ግንዛቤ ማስፊያ ስብሰባዎችን ማዘጋጀት • ተግባር 2. የት/ቤት ድጎማ በጀትን በሚመለከት የወላጆችና የህብረተሰብ ግንዛቤ ለማስፋት የሚያስችሉ ስብሰባዎችን ማዘጋጀት • ተግባር 3. ከት/ቤት የድጎማ በጀቱ ጋር የተያያዙ ሰነዶችን ማሻሻልና አደራጅቶ ማስቀመጥ፡፡ • ተግባር 4.በት/ቤት መሻሻል ዕቅድ የልዩ ፍላጎት ትምህርት ጉዳዮችን ማካተት (ልዩ ፍላጎት ያለባቸው ህጻናት ካሉ)፡፡ • ተግባር 5. የትምህርት ቤት ድጎማ በጀት ገንዘብን መቀበል • ተግባር 6. የትምህርት ቤት መሻሻል እቅዱን በሥራ ላይ ማዋል • ተግባር 7. አጠቃላይ የሂሳብ ሪፖርትና የት/ቤት የድጎማ በጀት ማስታወቂያ ሰሌዳ ለሕዝብ ማዘጋጀት

አባሪ 2፡ የት/ቤት የሂሳብ ሪፖርት ቅጽ

የት/ቤቱ ስም፡-	የት/ቤቱ ርዕሰ መምህር፡-
ክልል፡-	የት/ቤቱ ወ.ተ.መ.ህ. ሊቀመንበር
ዞን፡-	ጠቅላላ የት/ቤት የድጎማ በጀት መጠን፡-
ወረዳ፡-	የት/ቤት በጀት ገቢ የሆነበት ቀን፡-
ኦዲት የተደረገበት ቀን፡-	የበጀት ዘመን፡-

ማስታወሻ፡- ለማንኛውም ጥያቄ መልስዎ 'አይደለም' ከሆነ፣ እባክዎትን ምክንያቱን ይግለፁ				
ተ.ቁ.	መመዘኛ	አዎ (አ)	አይደለም (አይ)	አስተያየት
	የስራ እቅድ)			
	በት/ቤቱ የዘተጋጀ የት/ቤት ሥራ እቅድ አለ?			
	የሥራ እቅዱ የተዘጋጀው ከወ.መ.ህ እና ህብረተሰብ ጋር በመተባበር ነው?			
	የሥራ እቅዱ ጸድቋል?			
	የሒሳብ አሠራሮች			
	የሂሳብ መዝገቡ በተለመደው የሂሳብ መዝገብ አያያዝ በተለመደው የሂሳብ መዝገብ አያያዝ መሰረት በአምዶች ተከፋፍሎ የተዘጋጀ ነው?			
	በሒሳብ መዝገብ ላይ ቀኖችና ዓላማ /መግለጫዎች በአግባቡ በቦታቸው ተመዝግበው ይገኛሉ?			
	ገቢዎች በሂሳብ መዝገቡ ላይ በቦታቸው የሰፈሩ ናቸው?			
	ወጪዎች/ክፍያዎች በሂሳብ መዝገቡ ላይ በተገቢው ቦታቸው ተመዝግበዋል?			
	የሂሳብ መዝገቡ በየጊዜው መመሳከሩ ይረጋገጣል?			
	የት/ቤቱ ርዕሰ መምህር ቀሪ ሒሳቡን በየጊዜው ያረጋግጣል? እንዲሁም በሂሳብ መዝገቡ ላይ ርዕሰ መምህሩ ይፈርማል?			
	የስራ እቅድ)			
	ከ15,000 ብር የሚበልጥ የድጎማ በጀት ላላቸው ት/ቤቶች የባንክ ሂሳብ ተከፍሎቶላቸዋል?			
	በዓይነት የተደረጉ ገቢዎች ተመዝገበዋል (በማስተወሻዎችና በመዝገብ ላይ)?			
	ገቢና ወጪን ማመሳከር			
	ለገቢዎችና ወጪዎች ደጋፊ ሰነድ ተያይዞ ቀርቧል?			
	ወጪዎች በሚመለከተው ኃላፊ ፈቃድ ተሰጥቶባቸዋል?			
	ወጪዎች የተደረጉት በፀደቀ ዕቅድ መሠረት ነው?			
	አጠቃላይ			
	የሂሳብ መዝገቡ/ሪፖርቱ ለማህበረሰብ አባላትና ለሌሎች ሃላፊዎች ቀርቧል?			
	ይህ ሪፖርት በቃለ ጉባኤው መዝገብ ላይ እንዲሰፍር ተደርጓል?			
	ት/ቤቱ የሂሳብ ሪፖርትና ተዛማጅ የት/ቤቶች ድጎማ በጀት ጉዳዮች የሚለጠፉበትና በጉልህ የሚታይ የማስታወቂያ ሰሌዳ አለው (ቅፅ 6)?			

አስተያየጥት፡- በኦዲተሩ አስተያየት መሰረት ት/ቤቱ በትምህርት ቤት የድጎማ በጀት መመሪያ እና ፕሮግራም መመሪያው ላይ ባሉት ደንቦች መሰረት ማስተካከያ አድርጓል፡፡		
የት/ቤት ኦዲት ያካሄደው/ያዘጋጀው፡-		
ስም	**ፊርማ**	**ኃላፊነት**
የት/ቤት ኦዲቱን የመረመረው/የረጋገጠው፡-		
ስም	**ፊርማ**	**ኃላፊነት**
የት/ቤት ኦዲቱን ያፀደቀው፡-		
ስም	**ፊርማ**	**ኃላፊነት**

አባሪ 3. የትምህርት ቤት ድጎማ በጀት መመደቢያ ቅፅ

ክልል		በወረዳ ትምህርት ጽ/ቤት ወይም በወረዳ ፋ.ኢ.ል.ጽ/ቤት የት/ቤቶችን ድጎማ በጀት የሚከታተል ሃላፊ ስም፡-	
ዞን			
ወረዳ		በወረዳ ትምህርት ጽ/ቤት ወይም በወረዳ ፋ.ኢ.ል.ጽ/ቤት የት/ቤቶችን ድጎማ በጀት የሚከታተል ሃላፊ ፊርማ፡-	

ኮድ	ሀ	ለ	ሐ	መ	ሠ	ረ	ሰ	ሸ	ቀ	በ	ተ

ተ.ቁ.	የተቋሙ ስም	የተቋሙ ዓይነት (የመ/ ደረጃ ት/ቤት፣ 2ኛ ደረጃ ት/ቤት፣ አ.መ.ት.ማ.)	ከትምህርት አመራር መረጃ ሥርዓት የተገኘ የተማሪዎች ብዛት በደረጃ					ጠቅላላ 'መደበኛ' የት.ድ.በ. (ብር)	ከ200 ተማሪዎች በታች ስላሉት ተጨማሪ የት.ቤ.ድ.በ. አለው? (አዎ/አይደለም) (ብር)	ለልዩ ፍላጎት ተጨማሪ የት.ድ.በ. አለው? (አዎ/አይደለም) (ብር)	ጠቅላላ የተመደበው የት.ቤ.ድ.በ. ድምር (ብር)
			ከ1-4	ከ4-8	አ.መ.ት.ማ.	ከ9-10	ከ11-12				
			(50 ብር)	*(55 ብር)*	*(50 ብር)*	*(60 ብር)*	*(70 ብር)*				
								ሸ = (ሐ*50) + (መ*55) + (ሠ*50) + (ረ*60) + (ሰ*70)	ከአጀንዳ ቁ.1	ከአጀንዳ ቁ.2	ተ+በ = ሸ+በ (ከ200 ተማሪዎች በላይ ላሉዋቸው ተቋማት ተ+በ = ቀ+በ (ትንሽ ተቋም ከሆነ)

የወረዳ ሃላፊዎች እንደ አስፈላጊነቱ ወረቀት/ገጽ መጨመር ይችላሉ

አባሪ 4: የት/ቤት የቅድሚያ ትኩረቶች መለያ/ዝርዝር ማሳያ ቅጽ

የት/ቤቱ ሥም			
ወረዳ			
ዞን			
ክልል			
ጊዜ		እስከ	
ያዘጋጀው ሰው ስምና ፊርማ			
ያፀደቀው ሃላፊ ስምና ፊርማ			

ተ.ቁ..	በት/ቤት መሻሻል ዕቅድ ላይ ከማህበረሰብ ጋር በተደረገ ውይይት የቅድሚያ ትኩረት የሚሰጣቸው ተግባራት (ተግባር 2፣ አጀንዳ 3)	የሚገመተው ወጪ (ብር)	ሥራው የሚጠናቀቅበት ጊዜ	የመማር ማስተማር ር/ጉዳይ (አዎ / አይደለም)
1				
2				
3				
4				
5				

አባሪ 5:የሁለተኛው ምዕራፍ አጠቃላይ ትምህርት ጥራት ማሻሻያ ፕሮጀክት የት/ቤቶች ድጎማ በጀት የሂሳብ መዝገብ ቅጽ

የት/ቤቱ ስም		የገንዘብ ያዥ ስም	
ወረዳ		ወር	
ክልል		ዓ.ም.	

የእቃው መለያ/ቁ	ቀን	የከፋይ ስም	ክፍያው እንዲፈፀም የፈቀደው	የት/ቤቶች ድጎማ በጀት መጠን	ክፍያ					Balance	
					ጥገና	ግንባታ	የጽሕፈት መሣሪያ	የትምህርት መርጃ መሣሪያዎች	ሌላ	ብር	ሣ
የመጀመሪያ ሂሳብ ባላንስ (Opening Balance b/f)											
ድምር											

ሂሳቡን የሠራው/ያዘጋጀው		ሂሳቡን የመረመረውና ትክክለኛነቱን ያረጋገጠው	
በእጅ/በካዝና የሚገኝ ገንዘብ		የት/ቤቱ ርዕስ መምህር	
በባንክ የሚገኝ ገንዘብ		የሂሳብ ሠራተኛ/Accountant	
ድምር		ገንዘብ ያዥ	

አባሪ 6: :የሁለተኛው ምዕራፍ አጠቃላይ ትምህርት ጥራት ማሻሻያ ፕሮጀክት የት/ቤቶች ድጎማ በጀት ማስታወቂያ ሰሌዳ ቅጽ

የት/ቤቱ ስም	ወረዳ	ክልል	በዚህ ዓመት ት/ቤቱ የተረከበው የት/ቤቶች ድጎማ በጀት መጠን	የተረከበበት ቀን	ባለፈው ዓመት ት/ቤቱ የተረከበው የት/ቤቶች ድጎማ በጀት መጠን	የተረከበበት ቀን
			ብር:	/ /	ብር:	/ /

በት/ቤቶች ድጎማ በጀት የተሠሩ ሥራዎች		
የተሠራው ሥራ/ተግባር ዝርዝር መግለጫ	ሥራው/ተግባሩ በት/ቤት መሻሻል ዕቅድ እና የቅድሚያ ትኩረት መመዝገቢያ ቅጽ ላይ የነበረ ነው? (አዎ/ አይደለም)	ሥራው/ተግባሩ በት/ቤት መሻሻል ዕቅድ የመማር ማስተማር ርዕሰ ጉዳይ የተካተተ ነው? (አዎ/ አይደለም)
ከት/ቤቶች ድጎማ በጀት ውጭ በሌላ በጀት የተከናወኑ ዋና ዋና ተግባራት (የማህበረሰብ መዋጮን ጨምሮ)		
የተሠራው ሥራ/የተግባሩ ዝርዝር መግለጫ	ሥራው/ተግባሩ በት/ቤት መሻሻል ዕቅድ እና የቅድሚያ ትኩረት መመዝገቢያ ቅጽ ላይ የነበረ ነው? (አዎ/ አይደለም)	ሥራው/ተግባሩ በት/ቤት መሻሻል ዕቅድ የመማር ማስተማር ር/ጉዳይ የተካተተ ነው? (አዎ/ አይደለም)

ከላይ ከተጠቀሰው በተጨማሪ የማስታወቂያ ሰሌዳው የተሞሉ የት/ቤቶች ድጎማ በጀት ቅድሚያ ትኩረቶች ቅፅ (ቅፅ 4) እና የት/ቤት የሂሳብ ሪፖርት ቅጽ (ቅፅ 2) መያዝ ይኖርበታል፡፡